# «ሳይፋቱ» (ዲ ፋክቶ) ፍቺ*

*ፊልጶስ ዓይናለም* *

***መግቢያ***

ለጋብቻ የሕግ ጥበቃ የሚደረግባቸው ጊዜያት በሦስት የተከፈሉ ናቸው:: እነዚህም ጊዜ ያት በጋብቻ አፈፃፀም፣ በጋብቻ ዘመን እና በፍቺ ጊዜ ተብለው ተከፋፍለዋል[1]:: በዚህ ጽሑፍ ጥናት የሚደረግበት ጉዳይ ጋብቻ በፍቺ ጊዜ በሚኖረው የሕግ ጥበቃ ዙሪያ ይሆናል:: ይህ ተግባር የፍ/ቤቶችን ጣልቃ ገብነት የሚጠይቀውም በአብዛኛው ከፍቺ ጋር የተያየዘ የንብረት ጉዳይ ክርክር ስለሚከሰት ነው::

በጋብቻ የሚቋቋመው ቤተሰባዊ ግንኙነት እንደየሁኔታው በተጋቢዎቹ፣ በልጆቻቸው፣ በቤተዘመዶቻቸውና በማኅበረሰቡ ላይ ግላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብትና ግዴታን የመፍጠር ውጤት አለው:: በመሆኑም ጋብቻን መሠረት አድርጐ ከጋብቻ ውጤት ጋር ግንኙነት ያላቸውን መብቶችና ግዴታዎች ለማስከበርና ለመጠየቅ በተጋቢ ዎች፣ ወራሾችና በተለያዩ ሰዎች መካከል በርካታ አለመግባባቶችና ክርክሮች የሚዘወተሩ መሆኑን የፍ/ቤቶች መድረኮችና መዛግብት ይመሰክራሉ:: ፍ/ቤቶች ከሚቀርቡ ጉዳዮች ዓይነትና ብዛት አንፃርም መረዳት እንደሚቻለው በመቶኛ ስሌት ሲመዘን ጋብቻና ፍቺን ምክንያት አድርገው የሚቀርቡ ክርክሮች የመጀመሪያውን ድርሻ የሚይዙ ናቸው::

በሁሉም ፍ/ቤቶች የሚቀርቡ ቤተሰብ ነክ በተለይም ጋብቻና ፍቺን የሚመለከቱ ጉዳዮች ከፍሬ ነገር፣ ከማስረጃና ከሕግ ክርክር አልፎ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ሞራላዊ፣ ስሜታዊ፣ ወዘተ... ገጽታዎች የሚንፀባረቁበት በመሆኑ የክርክሩ አመራርና የውሣኔ አሰጣጥ ከፍተኛ እውቀት፣ ክህሎትና ጥንቃቄን የሚጠይቁ ናቸው:: ይሁንና የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92[2] መነሻ በማድረግ ፍቺና ውጤቱን በተመለከተ ለሚነሱ ክርክሮች የተለያዩ ፍ/ቤቶች የሚሰጧቸው ውሣኔዎች ሁለት ጽንፍ ሲይዙ ይስተዋላሉ:: ይህም የውሣኔ አሰጣጥ ልዩነትና ችግር ከፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲሁም በክልል ፍ/ቤቶች

---

* ኤል ኤል ቢ፣ ኤል ኤል ኤም፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኛ፣ እና በቅድስት ማርያም ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ሕግ ፋኩልቲ መምህር

**«ሳይፋቱ» /ዲ ፋክቶ/ ለጽሑፉ ርዕስ የተመ ረጠበት ምክንያት በተግባር / በእውነታው የተ ፋቱ ባልና ሚስት በሕጉ ድንጋጌ መሠረት ግን ያልተፋቱትን ውጤቱንና ተግባሩን የሚፈተ ሽበት በመሆኑ ነው:: ይህንን ሁኔታ የእንግሊዝኛው ንባብ በሚገባ ሁኔታ ይገልጸዋል::

- *De facto* : actual ; existing in fact ; having effect even though not formally or legally recognized. As opposed to
- *De jure* - as a matter of law ; existing by right or according to law.

[1] ለዚህ ማስረጃ አምስት ምንጮች ይጠቀሳሉ እነሱም:-

- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት፣ 1987 ዓ.ም፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ አንደኛ ዓመት ቁጥር 1 አንቀጽ 34/1/
- የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ፣ አዋጅ ቁጥር 213/92 /መግቢያና የዝርዝር ድንጋጌዎች አጠቃላይ ግንዛቤ/ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ልዩ ዕትም ቁጥር 1/1992
- የሰብአዊ መብቶች ሁሉ ዓቀፍ መግለጫ/1948 እ.ኤ.አ/፣ ዓለም አቀፍ ኢኮኖሚክ ሶሻል እና ባህላዊ መብቶች ስምምነት እና ዓለም አቀፍ የሲቪልና ፖለቲካዊ መብቶች ስምምነት፣ /1966 እ.ኤ.አ/ አንቀጽ 16/1/፣ 10/1/ እና 23 ለሦስቱም በቅደም ተከተላቸው

[2] ካሁን በኋላ በጽሑፉ ውስጥ በሌላ መልኩ ካልተገለጸ በስተቀር የቤተሰብ ሕጉ ወይም ሕጉ ተብሎ ወይም በአንቀጽ የሚገለጸው የተ ሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 መሆኑን ልብ ይሏል::

ጭምር የሚታይ መሆኑን ለማሳየት በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ለአብነት ምልከታ የሚደረግባቸው ጉዳዮች ቀርበዋል፡፡

የዚህ ጽሁፍ መሠረታዊ ጭብጥ ባልና ሚስት ያለ ፍ/ቤት ውሳኔ ለዓመታት ተለያይተው የግል ሕይወታቸውን ሲመሩ ከቆዩ በኋላ በፍ/ቤት የፍቺ ውሳኔ ወይም አንደኛው ተጋቢ ሲሞት ሚስትነት (ባልነት) እንዲረጋገጥላቸው የሚጠይቁትን ይመለከታል፡፡ ጽሑፉ በአጠቃላይ የመነሻ ሃሣብ ይጀምራል፡፡ በመቀጠልም ስለ ጋብቻ በፍቺ መፍረስ አግባብነት ያላቸውን የቤተሰብ ሕጉን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ትንተና ተደርጓል፡፡

በጽሑፉ ርዕስ ጭብጥ ዙሪያ በሀገራችን የሕግና ዳኝነት ሥርዓት ከ1952 ዓ.ም የፍትሐብሔሩ የቤተሰብ ሕግ መውጣት በፊትና በኋላ እንዲሁም ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ መውጣት ወዲህ ያለው ሥርዓትና ውጤቱ በዋናነት ንፅፅራዊ ፍተሻ ቀርቧል፡፡ የመጨረሻው የጽሑፉ ክፍል በሕግ መሠረት ሳይፋቱ በእውን (ዲ ፋክቶ ግን) ለብዙ ዓመታት (ከፍ/ቤቶች ጉዳዮች ለማየት እንደሚቻለው ከ4 እስከ 50 ዓመታት) ተለያይተው የኖሩ ጋብቻ ፈጽመው የነበሩ ወንድና ሴት አንዱ ሲሞት ወይም፣ በሚያቀርቧቸው የፍቺ ወይም የሚስትነት/ባልነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄዎች ላይ ያተኩራል፡፡ የተለያዩ ደረጃ ፍ/ቤቶች በዚህ ጭብጥ ላይ በሰጡዋቸው ውሣኔዎች ላይ ሕጉንና አተገባበሩን /አተረጓጐሙን ከውጤታቸውና ከግለሰቦች መብትና ግዴታዎች አንፃር ምልከታ በማድረግ ጽሑፉ የማጠቃለያና የመፍትሔ ሃሣቦችን ይሰነዝራል፡፡

## 1. አጠቃላይ የመነሻ ሃሣብ

### 1.1 ቤተሰብ የኅብረተሰብ መሠረት ስለመሆኑ

ከጥንታዊ ግሪስ ፈላስፋዎች፣ ፕላቶና አሪስቶትል የሕግ መሠረታዊ ዓላማ የኅብረተሰብን ግንኙነት ሥርዓት ማስያዝና መጠበቅ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡[3] ልማዶችና ባህሎች በተግባር በሕግ አውጭ ከሚወጡት ሕጐች በላይ ኃይል እንዳላቸው አበክረው ማመልከታቸውም ይታወቃል፡፡[4] "General Jurisprudence of Law and Society" በሚለው መጽሐፋቸው ስለ ሕግና ኅብረተሰብ ግንኙነት ምርምራቸውን የፃፉት ብራይን ታማናሃ (ሎቄሽሮቃ ማሮቂሮቃሮሻሮ) ሕግ የማኅብረሰብ ነፀብራቅ /መስታወት መሆኑን፣ ዓላማውም የኅብረተሰብን ግንኙነት በሥርዓት መምራት መሆኑንና ሕግ ይህንን ዓላማ የሚያሳካውም የኅብረተሰቡ ግንኙነት የሚመራበትን ደንቦች /ሕግ በማውጣት/ በመደንገግ/፣ በማስፈፀምና አለመግባባቶችን በመፍታት መሆኑን ያሰምሩበታል[5]፡፡

ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች እና የሲቪልና ፖለቲካዊ መብቶች ስምምነቶች «ቤተሰብ» በግልጽ ትርጉም ያልተሰጠው ሲሆን በይዘቱ የኅብረተሰብ የተፈጥሮ መሠረታዊ መነሻ እንደሆነና ከኅብረተሰብና ከመንግሥት ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ ተቋም መሆኑ ተገልጿል፡፡[6] በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 34 እና በቤተሰብ ሕጉ መግቢያም የቤተብ ምንነት የተገለፀው ከዓለም አቀፍ ስምምነቶች ድንጋጌዎች ጋር በተስማማና በተመሣሣይ ሁኔታ ነው፡፡ እነዚህ አገላለጾች «ቤተሰብ» የኅብረተሰብ /የሕዝብ/ መሠረታዊ መነሻ መሆኑን አጉልተው የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡

የቤተሰብ ሕግ ዓላማው በሕገ መንግሥቱ የተደነገገውን በጋብቻ አፈፃፀም፣ በጋብቻ ዘመንና በፍቺ ጊዜ የቤተሰብ ወይም የቤተሰብ አባላትን መብት እንዲከበር ማድረግ

---

[3] Brain Z. Tamanaha, A General Jurisprudence of law and Society ( New York, Oxford University Press, 2001) P.9

[4] ዝኒ ከማሁ ገጽ 13

[5] ዝኒ ከማሁ ገጽ 12

[6] ከላይ በቁጥር 1 የተገለጹት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች

ነው::[7] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግና የክልሎች የቤተሰብ ሕግጋትም ይህንን ዓላማና ግብ ይዘው መውጣታቸውን በየሕጐቹ መግቢያ ያበሥራሉ:: ከቤተሰብ ሕግ ዓላማ መካከልም አንደኛው መሠረታዊ ጠቀሜታው የኅብረተሰብ የተፈጥሮ መነሻ በሆነው በቤተሰብ ውስጥ /በአባላቱ መካከል/ የሚነሱ አለመግባባቶችን ፍትሐዊ በሆነና በተቀላጠፈ ሁኔታ ብቃት ባለው አካል እንዲዳኙ ማድረግ መሆኑን በየሕግጋቱ መግቢያ ተገልጿል:: በተለይም ከተጋቢዎቹ መብትና ግዴታ አንፃር የሕጉ ዓላማ ግላዊና የንብረት ግንኙነታቸውን በሥርዓት መምራት መሆኑን ከሕጉ ዝርዝር ድንጋጌዎችና አጠቃላይ መርሁ ግንዛቤ የሚወሰድበት ጉዳይ ሲሆን በሕገ መንግሥቱም በዚሁ መልኩ ተቀርጿል::[8] በሕገ መንግሥቱ ዲሞክራሲያዊ መብቶች በሚለው ክፍል ከተደነገጉት መብቶች መካከል አንደኛው "የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብቶች" በሚል በአንቀፅ 34 የተደነገገው መሆኑም ይታወቃል:: የቤተሰብ ሕግጋት የሚወጡትም ይህንን ሕገ መንግሥታዊ መብት ከሕገ መንግሥቱ ጋር ለማጣጣም፣ ለማክበርና ለማስፈፀም እንዲቻል ልዩ ሕግ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ ነው::[9]

በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት የግልና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎቹ ፈቃድ በሃይማኖቶች ወይም በባህሎች ሕጐች መሠረት መዳኘትን እንደማይከለከልና ዝርዝሩ በሕግ እንደሚወሰን በአንቀፅ 34 /5/ ተደንግጓል:: ይሁን እንጂ የቤተሰብ ሕጉ (የክልሎችንም የቤተሰብ ሕግጋት ጨምሮ) የቤተሰብ ነክ ክርክሮችን ለምሣሌ የፍቺና የፍቺ ውጤቶችን በተመለከተ ክርክር የተነሣ እንደሆነ የመወሰን ሥልጣኑ የፍ/ቤት ብቻ መሆኑን በአስገዳጅነት ደንግጓል::[10]

በሀገራችን ዘመናዊ የቤተሰብ ሕግ ከመውጣቱ በፊት ለምሳሌ ያህል፣ ፍትሐ ነገሥት ለጋብቻ ትርጉም ሰጥቶት ነበር:: ይኸውም «ጋብቻ  ማለት በእውነተኛ ምስክር አንድ ለማድረግ በሚሆን የካህናት ጸሎት በስምምነት ለመኖር ፍላጐታቸውን ስለማግኘት በሚረዳዱ፣ ገንዘብ ሃብትን ለማግኘት ከእነርሱም በኋላ የሚተካ ልጅ በአንድነት ለመውለድ በግልጽ ስምምነት የባልና ሚስት መስማማት ነውካ[11] የሚል ነው::

ይህ በከፊል የኢትዮጵያ ቀዳሚ ሕግ የነበረው ፍትሐ ነገሥት ስለጋብቻ ዓላማ ሲናገር ካየመጀመሪያው ሥራ ዘር ለመተካት ልጅ ለመውለድ መሆኑንና ሁለተኛው ሰው በእንስሳዊ ባሕርይው የፈቲው ፆር በፀናችበት ጊዜ ከእርሱ የሚገኝበት የሩካቤ ፍላጐት ይፈፀም ዘንድ መሆኑን (ፍትዎትን ለማራቅ)፤ ሦስተኛው ለመረዳዳትና አንድ ለመሆንካ[12] ስለመሆኑ በዝርዝር  ከማብራሪያና የቅዱሣት መፃሕፍት ማጣቀሻ ጋር ይገልፃል::

የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ሲረቀቅ በፍትሕ ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ በነበረው ረቂቅ አንቀፅ 31 "ጋብቻ አንድ ወንድና አንዲት ሴት በእኩልነትና በፈቃደኝነት ቤተሰብ ለማቋቋም የሚመሠርቱት ጥምረት ነውካ የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል::[13] ነገር ግን በሕግ አውጭው ጸድቆ የወጣው ሕግ የጋብቻን ትርጉም የሚገልጽ ድንጋጌ አላካተተም:: ይህ የሆነበትንም ምክንያት በሕጉ አርቃቂ ኮሚቴ አባልነት የተሳተፉት አቶ መሐሪ ረዳኢ "የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ ለመገንዘብ የሚረዱ አንዳንድ ነጥቦችካ በሚለው መጽሐፋቸው:-

---

[7] የፌዴራሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 34 እና የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ መግቢያ

[8] የፌዴራሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 10 እና አንቀጽ 34

[9] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ መግቢያ

[10] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 115 - 117 የክልሎችም የቤተሰብ ሕግጋት ተመሳሳይ ድንጋጌዎች አከትተዋል፣ ከታች ማስታወሻ ቁጥር 74-79 ይመልከቱ

[11] በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ትንሳኤ የመጻሕፍት ማተሚያ ድርጅት ፣ ፍትሐ ነገስት ንባብና ትርጓሜ/ አምስተኛ እትም/፣ ገጽ 223-224

[12] መጽሐፈ ሕግጋት ዓበይት፣ ስለ ጋብቻ/ ብርሃንና ሰላም አዲስ አበባ 1962 ዓ.ም/ ገጽ 206.

[13] መሐሪ ረዳኤ /ረዳት ፕሮፌሰር/ የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ ለመገንዘብ የሚረዱ አንዳንድ ነጥቦች /1995 ዓ.ም /ቅጽ 1 ገጽ 169.

«በትርጉም መልክ የሚቀረፀው አንቀፅ የጋብቻን ሙሉና ዋነኛ ይዘቶችን በአጥጋቢ ሁኔታ ሊገልጽ ስለማይችል ትርጉም ከመስጠት በመታቀብ አጠቃላይ ትርጉሙ ከተለያዩ የሕጉ አንቀጾች ግንዛቤ ሊወሰድበት እንደሚችል በመታመኑ ጋብቻን የሚተርጉም አንቀጽ አስፈላጊ አልሆነም» [14]

በማለት የሕግ አውጭን ሃሣብ አመላክተዋል፡፡

### 1.2 ጋብቻ በተጋቢዎቹ ግላዊ ግንኙነት ላይ ስለሚኖረው ውጤት፣

ጋብቻ በተጋቢዎቹ ግላዊ ግንኙነት ላይ የሚያስከትላቸው መሠረታዊ ውጤቶች ከዚህ በታች ከ"ሀ" እስከ "መ" የተዘረዘሩት ናቸው፡፡

ሀ/ ባልና ሚስት እርስ በርሣቸው መከባበር፣ መተጋገዝና መደጋገፍ ያለባቸው ሲሆን ይህንን የሚቃረን ስምምነት ማድረግም በሕጉ የተከለከለ ነው (አንቀጽ 49)፡፡

ለ/ ባልና ሚስት በማናቸውም ረገድ የቤተሰብን ደህንነትና ጥቅም ለማስጠበቅ ልጆቻቸው በመልካም ሥነ ምግባር እንዲታነፁ ተገቢ ትምህርት እንዲቀስሙና ኃላፊነት የሚሰማቸው ዜጐች ሆነው እንዲያድጉ ለማድረግ በቤተሰብ አመራር የመተባበር ግዴታ ያለባቸው መሆኑ ... በሕጉ ተደንግጓል (አንቀጽ 50፣51)፡፡

ሐ/ ባልና ሚስት አብረው እንዲኖሩ የሕግ ግዴታ እንዳለባቸው፣ ለጤናቸው አደገኛ ካልሆነ በስተቀር ከጋብቻ የሚጠበቀውን የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም እንዳለባቸውና በሕጉ በተፈቀደው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ይህንን የሚቃረን ማናቸውም ስምምነት ውጤት እንደማይኖረው በሕጉ በአስገዳጅነት ተደንግጓል፡፡[15]

መ/ ባል ለሚስቱ ሚስት ለባልዋ ታማኝ የመሆን ግዴታ ያለባቸው መሆኑም ሌላኛው የጋብቻ ግላዊ ውጤት ነው (አንቀጽ 56)፡፡

በሀገራችን የቤተሰብ ሕግ የውጤቶች /የመብትና ግዴታዎቹ/ አለመሟላት ወይም መቋረጥ (ለምሣሌ አብሮ የመኖር ግዴታ ለረጅም ጊዜ ቢቋረጥ) በቤተሰብ ተቋሙ /በጋብቻው ም ሆነ በባልና ሚስቱ የግል መብትና ግዴታ ላይ ስለሚኖረው ውጤት የተካተተ ግልጽ ድንጋጌ የለም፡፡ በመሆኑም የጋብቻ ውጤቱን አክብረው ያሉና ያላከበሩ በተለይም ለዓመታት የጋብቻ በግላዊ ግንኙነት ላይ የሚኖረውን ውጤት አቋርጠው ከዚያም ሲያልፍ ሌላ ጋብቻ በመፈፀም ጭምር በሌላ የጋብቻ ውጤት እየተጠቀሙ የሚኖሩ በፍቺ ጊዜ እኩል መብት ሊኖራቸው ይገባልን? የጋብቻ ግላዊ ውጤትና በንብረት በኩል የሚኖረውስ ወጤት ምን ዓይነት ግንኙነት ይኖራቸዋል? የሚሉትና ሌሎች ተመሣሣይ ጭብጦች በጥልቀት መመርመር የሚገባቸው ነጥቦች ናቸው፡፡

### 1.3 ጋብቻ በንብረት በኩል ስለሚኖረው ውጤት

ሕገ መንግሥቱ "የንብረት መብት" በሚለው በአንቀፅ 40 ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ/ኗ/ እንደሚከበርለት/ላት/ ደንግጓል፡፡ ከንብረት ሕግና ከሌሎች ሕግጋት አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ለመረዳት እንደሚቻለው አንድ ሰው ሕጋዊ የንብረት ባለመብትነት የሚኖረው ንብረቱን በድካሙ አፍርቶና በውል፣ በስጦታ ወይም በውርስ አግኝቶ ወይም በሌላ በማናቸውም መልኩ በሕግ መሠረት በማግኘት ሊሆን እንደሚችል አጠቃላይ ግንዛቤ ይወሰድበታል፡፡ በቤተሰብ ሕጉ መሠረት ባልና ሚስት በጋብቻ ዘመናቸው የግል ወይም የጋራ ንብረት ሊኖራቸው እንደሚችል በሕጉ ተፈቅዷል፡፡

ሀ/ በጋብቻ ዘመን የባልና ሚስት የግል ንብረቶች ሆነው የሚቀሩት ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸው ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኋላ

[14] ዝኒ ከማሁ ገጽ 12

[15] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 53፤ ከዚህ ላይ ባልና ሚስት የሚኖሩበትን ስፍራ በጋራ የመወሰን ሥልጣን የተሰጣቸው ሲሆን በተወሰነ ወይም ባልተወሰነ ጊዜ ተለያይተው ለመኖር መስማማትም እንደሚችሉ በሕጉ ተመልክቷል፡፡ / አንቀጽ 54፣55/

በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው የሚያኙአቸው ንብረቶች ናቸው (አንቀጽ 57)፡፡ ይህም ሁኔታ ተፈፃሚነት የሚኖረው ንብረቶቹ በጋብቻ ውል የጋራ እንዲሆኑ ስምምነት ካልተደረገባቸው ብቻ ነው፡፡

ለ/ ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ በግብይት የሚያገኙአቸውን ንብረቶች ማለትም የግል ሃብቱ በሆነ ንብረቱ ለውጥ ያገኘው ወይም በግል ገንዘቡ የገዛቸው ወይም የግል ንብ ረቱን ሸጦ የሚያገኘው ገንዘብ የግል ይባልልኝ ብሎ አንደኛው ወገን ጥያቄ አቅርቦ በፍ/ቤት ካፀደቀው የግል ሃብቱ ይሆናል (አንቀጽ 58)፡፡

ሐ/ ባልና ሚስት በጋብቻ ዘመን እያሉ ከግል ንብረታቸውና ከግል ወይም ከጋራ ንብ ረታቸው የሚያገኙአቸው ገቢዎች ሁሉ የጋራ ሃብታቸው እንደሚሆኑ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 62 እና 63 ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ በግብይት የሚያገኙት ንብረት በፍ/ቤት የአንደኛው ተጋቢ የግል ሃብት ነው ካልተባለ በስተቀር፣ በስጦታ ወይም በኑዛዜ ለተጋቢዎቹ የተሰጧቸው ንብረቶች ሁሉ የጋራ ሃብቶቻቸው እንደሚሆኑ በአንቀጽ 58 እና 62 ተደንግጓል፡፡

መ. በሕጉ ግምት መሠረት አንደኛው ተጋቢ የግል ሃብቱ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር ማንኛውም ንብረት በአንደኛው ተጋቢ ስም ብቻ የተመዘገበ ቢሆንም እንኳን የጋራ ሃብት እንደሆነ እንደሚቆጠርም በሕጉ አንቀጽ 63/1/ በአስገዳጅነት ተደንግጓል፡፡

ሠ/ የግልና የጋራ ሃብት ማስተዳደርን በተመለከተ ሕጉ ለተጋቢዎቹ እንደ አግባብነቱ የግል ሀብት በግል፣ የጋራ ሀብትን በጋራና በውክልና ወይም ሌላ ሁኔታ በግል ለማስተዳደርና ገቢን ለመቀበል እንደሚቻል በዝርዝር ድንጋጌዎቹ አካትቷል፡፡ (የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ 59፣ 60፣ 61 እና 67 ይመለከቷል)፡፡

ረ/ የጋራ የሆነውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ፣ ለመለወጥ፣ ለማከራየት በመያዣ ወይም በዋስትና ለመስጠት ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ በንብረቱ ላይ ሌሎች ሦስተኛ ሰዎች መብት እንዲያገኙ ለማድረግ እንዲሁም በሌሎች ሁኔታዎች ጭምር፣ በልዩ ሁኔታ ቀሪ ካልተደረገ በስተቀር የተጋቢዎቹ የጋራ ስምምነት አስፈላጊ መሆኑም፣ አንደኛው ጋብቻ በተጋቢዎቹ የንብረት ግንኙነት ላይ ያለው ውጤት መሆኑን በሕጉ አንቀጽ **68** በዝርዝር ተደንግጓል፡፡ ስምምነቱ ከሌለ ግን እንደሁኔታው ግዴታው ሊፈርስ ይችላል፡፡

ሰ/ ጋብቻ በንብረት በኩል ዕዳንም የሚመለከት ውጤት አለው፡፡ ይኸውም ከባል ወይም ከሚስት የሚጠየቅ ዕዳ ከባለዕዳው ተጋቢ የግል ሃብት፣ የግል ሃብቱ ዕዳውን ለመሸፈን በቂ በማይሆንበት ጊዜ ከጋራ ሃብታቸው ሊከፈል ይችላል (አንቀጽ 70 (1))፡፡ ዕዳው የመጣው ለትዳራቸው ጥቅም ከሆነ ደግሞ ከጋራ ሃብታቸው፣ የጋራ ሃብታቸው ዕዳውን ለመሸፈን በቂ በማይሆንበት ጊዜ ከባል ወይም ከሚስት የግል ሃብት ሊከፈል እንደሚችልም በሕጉ ተመልክቷል (አንቀጽ 70(2))፡፡

ከዚህ ጽሁፍ ዓላማ አንፃር ሌሎችን የጋብቻ ውጤቶች መተንተን ሳያስፈልግ በግላዊ ግንኙነትና ንብረት ረገድ ያለውን የውጤቶች ዝምድና ቀጥለን በአጭሩ እንመለከታለን፡፡

## 2. የጋብቻ በግላዊ ግንኙነትና በንብረት በኩል ያለው የውጤቶች ዝምድና

ጋብቻ በተለይም በተጋቢዎቹ ላይ አካላዊ፣ መንፈሣዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስርን የሚፈጥር ነው፡፡ ይህም እውነታ በጥንታውያን ቅዱሣት መጽሐፍት ጭምር "ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት፣ እንደዚሁም ደግሞ ሚስት ለባልዋ፣ ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ እንዲሁም ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ" በሚል ተከትቦ ይገኛል፡፡[16] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ሲረቀቅ በፍትሕ ሚኒስቴር በተዘጋጀው ረቂቅ "ጋብቻ አንድ ወንድና አንዲት ሴት በእኩልነትና ፈቃደኝነት ቤተሰብ ለማቋቋም የሚመሰርቱት ጽም

[16] መጽሐፍ ቅዱስ 1ኛ ቆሮ. ቁጥር 7÷4-5

ረት ነው"[17] በማለት መተርጐሙም ጋብቻ ልዩ ትስስርን የሚፈጥር መሆኑን የሚያስገነዝብና ከጥንታዊው መጽሐፍ አገላለጽ ጋር የሚስማማ ነው፡፡

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ረቂቅ ላይ በተካሄዱት አውደ ጥናቶች ተሣታፊ የነበሩት አንዳንድ የሃይማኖት አባቶች ጋብቻ ተጋቢዎችን ራሣቸውን ብቻ ሳይሆን ንብረታቸውን ገንዘባቸውን የሚያቀላቅል ተፈጥሮአዊና አምላካዊ ተግባር መሆኑን አበክረው ይገልፁ እንደነበር ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡[18] በዚህ እምነት መሠረትም ጋብቻ ሌላ ተጨማሪ ድርጊት ወይም ሥርዓት ሳያስፈልገው በመፈጸሙ ብቻ የጋራ ንብረት ባለቤትነት ይፈጥራል፣ የሚል አስተሳሰብ ይታያል፡፡ በሌሎች ሃይማኖቶችና ባህሎች መሠረት ደግሞ ጋብቻ ተጋቢዎችን አንድ ሥጋ» ያደርጋል እንጂ በንብረታቸው ላይ የሚያስከትለው ውጤት አይኖርም፣ ንብረታቸውን በተመለከተ በጋብቻ ውል የሚገዛ ይሆናል ይላሉ፡፡[19]

የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ጋብቻ በግላዊ ግንኙነት ላይ እና በንብረት በኩል ያለውን የውጤት ግንኙነት በግልጽ አያመላክትም፡፡ ከዚህ ጭብጥ ጋር በተያያዘ መልኩ አቶ መሐሪ ረዳኢ ስለጋብቻ ውጤት ሲያብራሩ "ጋብቻ በመፈፀሙ ብቻ የጋራ ባለሃብትነት መብት እንደማይፈጥር... በጋብቻ ዘመኑ በየግል የሚገኝ የባልና ሚስት ገቢ ወይም ሃብት የጋራ የተባለበት ምክንያት በገቢው /በሃብቱ መፈጠር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሌላኛው ተጋቢም አስተዋጽኦ አለው ተብሎ ስለሚታመን ይህን ገቢ የጋራ ሃብት ማድረግ አግባብ ነው ተብሎ ስለሚታመን" መሆኑን አስምረውበታል፡፡[20] አያይዘውም በሕጉ ዓይን ጋብቻ በመፈጸሙ ብቻ የጋራ ንብረትን ይፈጥራል የሚለው የአንዳንድ ሃይማኖቶችና ባህሎች አቋም የሕግ መሠረት ያለው አለመሆኑን በአጽንኦት ይገልፃሉ፡፡[21]

የሕጉ አርቃቂ ኮሚቴ አባል የሆኑት አቶ መሀሪ ባልና ሚስት ጋብቻ ፈጽመው በጋብቻቸው ግላዊ ግንኙነት ሳይጸኑ ነገር ግን ጋብቻውን በፍ/ቤት ውሣኔ ሳያፈርሱ ለብዙ ዓመት ቢለያዩ መለያየታቸው በጋብቻው የንብረት ውጤት ላይ የሚያመጣው ለውጥ ይኖር ይሆንን? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ ከላይ የተገለጸውን ሃሣብ በማጠናከር፡

> «በመሠረቱ ጋብቻ በፍቺ የሚፈርሰው ፍ/ቤት የፍቺ ውሣኔ ሲሰጥ ብቻ ነው፡፡ ይሁንና ባልና ሚስቱ በዘላቂነት በተለያዩበት ዘመን በየግላቸው ያፈሩት ገቢ/ሃብት ፍቺ ባለመፈፀሙ ብቻ የጋራ ይሆናል ማለት አይቻልም፡፡ የሕጉም ዓላማና ግብ አይደለም፡፡ ጋብቻ በንብረት በኩል የሚኖረው ውጤት በግላዊ ግንኙነት ላይ ካለው ውጤት ጋር አብሮ መታየት አለበት»[22]

ይላሉ፡፡ ይህንን አስተሳሰብ ሌሎች በዩኒቨርስቲ የቤተሰብ ሕግ መምህራን[23] እና አንዳንድ ዳኞችም ይጋሩታል፡፡[24]

---

[17] ከላይ በቁጥር 13 የተመለከተው

[18] ዝኒ ከማሁ ገጽ 63

[19] ዝኒ ከማሁ

[20] ዝኒ ከማሁ ገጽ 67 እና 68

[21] ዝኒ ከማሁ ገጽ 64

[22] ከአቶ መሐሪ ረዳኢ /ረዳት ፕሮፌሰር/ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሕግ መምህር ጋር ህዳር 4 ቀን 2000 ዓ.ም በጽሑፉ ጭብጥ ዙሪያ ከተደረገ ውይይት የተወሰደ ሃሣብ ፣ እንዲሁም የፌ/መ/ደ/ ፍርድ ቤት ዳኛ ወ/ሮ አደይ ንጉሴም ይህንን ሃሣብ ይጋሩታል፡፡ (በ12/3/2000 ከተደረገ ወይይት የተወሰደ)

[23] ከአቶ መለሰ ዳምጤ /ረዳት ፕሮፌሰር/ በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ የሕግ መምህር፣ ከአቶ ኤልያስ ኑር በቅድስት ማርያም ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ የሕግ ፋኩልቲ ዲን እና አቶ አስቻለው አሻግሬ በአልፋ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ የሕግ መምህር ጋር ከህዳር 3 እስከ 5 ቀን 2000 ዓ.ም ባሉት ቀናት በጽሑፉ ጭብጥ ዙሪያ ከተደረገ ውይይት የተወሰደ ሃሣብ፡፡

[24] ከአቶ ጐሽዬ ዳምጠው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ዳኛ ጋር ከተደረገ ውይይት እና በዳኛው ከተሰጡ ፍርዶች የተወሰደ፡፡

በአንፃሩ ደግሞ «ጋብቻ ተፈጽሞ እስካልፈረሰ ድረስ የባልና ሚስቱ በዘላቂነት መለያየት ወይም በግላዊ ግንኙነት የጋብቻ ውጤት ጸንቶ አለመኖር፣ ጋብቻ በንብረት በኩል በሚኖረው ውጤት ላይ ምንም ልዩነት መፍጠር እንደማይችልና ጋብቻው እንደፀና ስለሚቆጠር የቤተሰብ ሕጉን አጥብቆ በመከተል በጋብቻው ዘመን በአንደኛው ተጋቢ በግል ጥረት የተገኘ ገቢ /ሃብት/ በሙሉ የባልና ሚስቱ የጋራ ሊሆን ይገባዋል» የሚለውን አስተሳሰብ የሚከተሉ ዳኞች መኖራቸውን ፀሐፊው ከዳኞቹ ጋር ባደረገው ውይይት ለመረዳት ችሏል፡፡[25] እነዚህ አቋሞች የግል አስተሳሰብ ብቻ ሣይሆኑ በክፍል "4" ምልከታ ለሚደረግባቸው በፌደራሉና በክልሎች ፍ/ቤቶች በተሰጡ ፍቺ ነክ ፍርዶችም በተግባር የሚታዩ ናቸው፡፡ ይህንን አስተሳሰብ የሚከተሉ ባለሙያዎች ጋብቻ በግላዊ ግንኙነትና በንብረት በኩል ያለውን ውጤት ለያይቶ በማየቱ ውጤት ላይ በመርህ ደረጃ አይስማሙበትም፡፡

ሕጉ በጋብቻ ዘመን በግል በሚገኝ ገቢ/ሃብት ላይ ለባልና ሚስቱ የጋራ የንብረት ባለሃብትነትን መብት የሚያጐናጽፈው የጋብቻው መፈፀምን ብቻ መሠረት አድርጐ ሳይሆን ጋብቻ በግላዊ ግንኙነት ላይ ያለውን የመረዳዳት፣ የመተጋገዝ፣ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነትን ...ወዘተ መሠረት አድርጐ ነው የሚለው አስተሳሰብ እንደ ፀሐፊው ግንዛቤ አሳማኝና ሎጂካዊ ነው፡፡ በመሆኑም ጋብቻ በግላዊ ግንኙ ነት ላይ ያለው ውጤትና በንብረት በኩል ያለው ውጤት የምክንያትና ውጤት ግንኙነት (Cause and effect relationship) አላቸው ብሎ መረዳቱ ምክንያታዊ አስተሳሰብ ነው፡፡

በአንዳንድ አገሮች የቤተሰብ የሕግ ሥርዓት ለምሣሌ በአሜሪካን የቤተሰብ ሕግ ከፍቺ በመለስ በባልና ሚስቱ መካከል ዘላቂ የሆነ መለያየት (Permanent Separation) መኖሩ ሲረጋገጥ ተጋቢዎቹ በተለያዩበት ዘመን በየግላቸው የሚያፈሩት ገቢ/ሃብት የግላቸው ሆኖ እንዲቀር መፈቀዱም[26] ከላይ የተመለከተውን አንደኛውን አስተሳሰብ የሚደግፍ ነው፡፡ በእኛስ ሀገር ለብዙ ዓመታት በቋሚነት የተለያዩ ተጋቢዎች የፍቺ ውሣኔ ሲጠይቁ ወይም ከሁለት አንደኛቸው ሲሞት በሕይወት የቀረው ከሚች ጋር ጋብቻ ለመኖሩ / ሚስትነት ወይም ባልነት / እንዲረጋገጥላቸው ሲጠይቁ ባመለከቱት መሠረት ሊወስንላቸው ይገባልን? የሚወሰንላቸው ቢሆንስ ተጋቢዎቹ በተለያዩበት ዘመን በግል በተፈራው ንብረት በኩል ጋብቻው የሚኖረው ውጤት እንዴት ይታያል? የሚለው ጉዳይ የዚህ ጽሁፍ መሠረታዊ ትኩረትና የሚቀጥሉት ሁለት ክፍሎች ደግሞ ዋነኛ ጭብጥ ነው፡፡

## 3. ፍቺና የአፈፃፀም ሥርዓቱ

### 3.1 አጠቃላይ የመነሻ ሃሣብ

ጋብቻ የሚቋቋምበት የአፈፃፀም ሥርዓት እንዳለው ሁሉ የሚፈርስበት የአፈፃፀም ሥርዓትም ያለው ለመሆኑ በሕጉ ተመልክቷል፡፡ ጋብቻው የተፈፀመበት ሥርዓት ማናቸውም ዓይነት ቢሆን የጋብቻው መፍረስና የሚያስከትለው ውጤት አንድ ዓይነት ስለመሆኑና የጋብቻውን መፍረስ በተመለከተ ማናቸውም ልዩነት እንደማይደረግም በቤተ ሰብ ሕጉ አንቀፅ 74 ተደንግጓል፡፡

ጋብቻ በሕጉ መሠረት የሚፈርስባቸው ምክንያቶች ሦስት ናቸው፡፡ እነሱም በሕጉ አንቀጽ 75 እንደተደነገገው፣

1. ከተጋቢዎች አንዱ ሲሞት ወይም በፍርድ ቤት የመጥፋት ውሣኔ ሲሰጥ ወይም

[25] ከአቶ ደረጀ ኢቲቻ የፌ.ከ.ፍ.ቤት ዳኛ፣ ከአቶ ዮሴፍ አፅምሮ የፌ.ከ.ፍ.ቤት ዳኛ እና ከአቶ ደስታ በርሄ የፌ.መ.ደ.ፍ.ቤት ዳኛ ጋር ከህዳር 5 - ህዳር 10 ቀን 2000 ዓ.ም ባሉት ቀናት ከተደረገ ውይይት የተወሰደ ነው፡፡

[26] Family Law in the Unites States Legal System, http://www.google.com (Visited on October 3, 2007 )

2. ጋብቻ ለመፈፀም መሟላት ካለባቸው ሁኔታዎች አንዱ በመጣሱ ምክንያት በሕግ መሠረት ጋብቻው እንዲፈርስ ሲወሰን ወይም
3. የፍቺ ውሣኔ ሲሰጥ ናቸው፡፡

ስለፍቺ ታሪክ የተፃፉ ሕግ ነክ ጽሑፎች እንደሚያስረዱት ፍቺ ለተጋቢዎቹ ነፃ ፈቃድ የተተወበት፣ ፍቺ በፍፁም የማይፈቀድበት /የማይቻልበት፣ ፍቺ በሃይማኖት አባቶች ውሣኔ የሚሰጥበት፣ ለፍቺ ከባድ ምክንያት የሚያስፈልግበት እንዲሁም ፍቺ እንደ መሠረታዊ መብት ተቆጥሮ ያለ ምንም ምክንያት የሚፈቀድበት ሥርዓቶች ነበሩ፡፡ አሁንም አሉ፡፡ ከጽሑፉ ይዘትና አድማስ አንፃር ጥቂቶቹን ለአብነት ለመጥቀስ ይቻላል፡፡

በጥንታዊው የሮማን የሕግ ሥርዓት በዓመተ ዓለም ዘመናት ጋብቻ የተጋቢዎቹን አብሮ የመኖር ስምምነትና ፈቃድ መሠረት ያደረገ ስለነበር በተመሣሣይ መልኩ የጋብቻ በፍቺ መቋረጥ በተጋቢዎች ወይም በአንደኛው ተጋቢ ነፃ ፍላጐት ሊፈፀም እንደሚችል የተፈቀደ ነበር፡፡[27] በዚህ የሕግ ሥርዓት መሠረት የፍቺ መፈፀምን ለማስረዳት አስፈላጊው ነገር የመፋታት ሃሣብ መኖሩን ማረጋገጥ ብቻ ነበር፡፡[28] ይሁንና በሕዝብ አስተያየት እና የቤተሰብ ሽምግልና ጉባኤ መቋቋም ምክንያት ከ307 ዓ.ዓ አካባቢ ጀምሮ ተጋቢዎች የነበራቸው የፍቺ ሙሉ ነፃነት እየጠበበ መምጣቱን ባሪ ኒኮላስ (Bary Nicholas) ገልጸዋል፡፡[29] በተለይ ደግሞ የሮማኑ ግዛት ክርስትናን እንደ ብሔራዊ ሃይማኖት ከመቀበሉ ጋር ተያይዞ ለፍቺ የነበረው አመለካከት ፍፁም ለውጥ በማምጣት ሮማውያን ስለ ፍቺ የነበራቸው ቀደምት አስተሳሰብ ተቀይሮ ፍቺ ለተጋቢዎቹ ነፃ ውሣኔ ብቻ መተው እንደሌለበትና የሃይማኖትም ጉዳይ መሆኑን በሮማ ጥንታዊ/ባህል ሕግ ሳይሆን በፍ/ቤት ውሣኔ መፈፀምም እደሚኖርበት የማስገደድ ሁኔታ መፈጠሩን የሮማዊያን የፍቺ ሕግ እድገት ታሪክ ያስረዳል፡፡[30]

በፈረንሣይ የሕግ ሥርዓት የፍቺ ጉዳይ የተለዋዋጭነት ታሪክ ያሳለፈ ሲሆን እስከ ፈረንሣይ አብዮት ድረስ ፍቺ በሕግ ያልተፈቀደበት፣ ከአብዮቱ በኋላ የተፈቀደበት፣ እንዲሁም በ1816 የካቶሊክ እምነት የመንግሥት ሃይማኖት በሆነበት ጊዜ ፍቺ የተከለከለበት፣ በቅርብ ዘመናት ደግሞ ለፍቺ ምክንያት የሚጠየቅበት ሥርዓት መታየቱን በሀገሪቱ የቤተሰብ ሕግ ታሪክ ላይ የተፃፉ ጽሑፎች ይመሰክራሉ፡፡[31] የጀርመን የፍቺ ሕግ ሥርዓትም እንደፈረንሣዩ ተለዋዋጭነት የታየበት ሲሆን በጥንታዊው ሕግ በሕግ መሠረት፣ በተጋቢዎቹ ወይም በአንደኛው ተጋቢ ፍላጐት በመሐከሉም ጥብቅ በሆነው ካቶሊክ ሃይማኖት መሠረት ከዝሙት በስተቀር ፍቺ የሚከለክል ሥርዓት በኋላም በፕሮቴስታንት ሃይማኖት መሠረት እና በዘመናዊው የመንግሥት ሕግ ለቀቅ ያለ የፍቺ ሕጐች ተስተናግደዋል፡፡[32]

ከላይ የተመለከቱትን የሮማን፣ የፈረንሣይ እና የጀርመን የፍቺ ሕግ ሥርዓት ተለዋዋጭነትን ሁኔታ የኢትዮጵያ የፍቺ ሕግ ሥርዓት ታሪክም ይጋራዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ክርስትና የመንግሥት ሃይማኖት በሆነበት ዘመን ሕጉ ስለ ፍቺ የነበረው አቋም በክርስትናው እምነት ደንብ የሚመራ ከዝሙት በስተቀር አይፈቀድም የሚል የነበረ ሲሆን በፍትሐብሔሩ የቤተሰብ ሕግ ከዝሙት በተጨማሪ ሌሎች የፍቺ ምክንያቶች የተገለፁ ከመሆኑ በቀር ባልና ሚስት ለመፋታት የነበራቸው መብት በፍትሐብሔር ሕጉ ውስጥ እጅግ የጠበበ ነበር፡፡ በአንፃሩ ደግሞ በአዲሱ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ

[27] Barry Nicholas, An Introduction to Roman Law, (Oxford, Clarendon Press, 1962), p.85
[28] ዝኒ ከማሁ
[29] ዝኒ ከማሁ
[30] ዝኒ ከማሁ ገጽ 85-87
[31] Maurice Shelden Amos and et a1. Introduction to French Law (Oxford, Clarendon press,1935), p.69
[32] Rudolf Huebner, A History of Germanic Private Law (The Law Book Exchange, Ltd. Union New jersey) p. 613-615

ምክንያት ሳይገልጹ የፍቺ ጥያቄ ቢቀርብ እንደ መሠረታዊ መብት ተቆጥሮ ሊፈቅድ ይችላል።

ይሁን እንጂ በሀገራችን በጥንትም ሆነ በዘመናችን በሕጉ ከተቀመጠው ደንብ ውጭ በተጋቢዎቹ ፍላጐትና ስምምነት በሽምግልና ወይም በልማድ ደንቦች መሠረት ፍቺ እንደሚፈፀም ከማህበራዊ እውነታዎች እና በፍ/ቤት ከሚቀርቡ ጉዳዮች ለማረጋገጥ ይቻላል።[33] ምን ያህሉ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ነው በፍ/ሕግና በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ብቻ ፍቺ ሲፈጽም የቆየው የሚለውን ጥያቄ በዚህ አጋጣሚ ማንሳት ተገቢ ይሆናል።

### 3.2 ፍቺ ምንድን ነው?

ስለጋብቻና ፍቺ የተፃፉ መንፈሳዊ፣ ማህበራዊና ሕግ ነክ ጽሑፎች ለፍቺ የሚሰጡት ትርጉም ተመሣሣይነት ያለው ነው። በአጠቃላይ ሁሉም የሚስማሙበት የፍቺ ትርጉም ጋብቻ የሚፈርስበት፣ የባልና ሚስት የጋብቻ ትስስር/ ጽምረት የሚቋረጥበት መንገድ መሆኑን ነው። የተሻሻለው ሕግ ለፍቺ ትርጉም ከመስጠት የተቆጠበ በመሆኑ ለሕጉ አተረጓጎም በሌሎች ጽሑፎችና በመዝገበ ቃላት የተሰጡትን ትርጉሞች መመልከቱ ተገቢነት ይኖረዋል።

በፈረንሣይ የሕግ ሥርዓት "ፍቺ በተጋቢዎቹ የሕይወት ዘመን ሕጋዊ ጋብቻ የሚቋረጥበት" መሆኑንና እያንዳንዱ ተጋቢ የግሉ ሕይወት እንዲኖር የሚፈቀድበት ሥርዓት ስለመሆኑ[34] ለጽንሰ ሃሣቡ ትርጉም ተሰጥቶታል። ከሌሎችም የተለያዩ ጽሑፎች ለመረዳት እንደሚቻለው ፍቺ የሕጋዊ ጋብቻ በሕግ መሠረት መቋረጥ፣ የጋብቻ ሁኔታ በሕጋዊ መንገድ የሚቋረጥበት ሁኔታና ሥርዓት፣ የባልና ሚስቱ በሕይወት እያሉ መለያየት ወይም ጋብቻቸውን ማፍረስ፣ የጋብቻ ትስስር /ጽምረት/ መቋረጥ. . . መሆኑን አጠቃላይ ግንዛቤ ተወስዶበታል።[35]

የጋብቻ በፍቺ መፍረስ ተጋቢዎች ልጆች ካላቸው አስተዳደጋቸውንና ቀለባቸውን እንዲሁም የተጋቢዎቹን የግልና የጋራ ንብረትን የሚመለከት ውጤት ይኖረዋል። በዚህ መሠረት ጋብቻ በተጋቢዎቹ ግላዊ ግንኙነት ላይ ያለው ውጤት በፍቺ ምክንያት ሙሉ በሙሉ የሚቋረጥ ሲሆን በንብረት በኩል በሚኖረው ውጤት መሠረት ደግሞ የንብረት ክፍፍል ተግባርን ያስከትላል።

### 3.3. የፍቺ አፈፃፀም ሥርዓት ከ1952 ዓ.ም የፍትሐብሔሩ የቤተሰብ ሕግ በፊት

ከ14ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እንደ መንፈሳዊና ሥጋዊ ሕግ ለማገልገሉ ታሪክ በመዘገበለት በአብዛኛው ምንጩ የክርስቲያን ሕግና ሥርዓት በሆነው ፍትሐ ነገሥት እንደ አጠቃላይ መርህ/ደንብ ፍቺን የሚከለክልና የሚያወግዝ የነበረ ሲሆን በልዩ ሁኔታ ግን በዝሙት ምክንያት ብቻ መፍታት እንደሚቻል የሙሴን መጽሐፍ ማጣቀሻ በማድረግ ይናገራል።[36] ይህ የፍቺ ሥርዓት በክርስትና ሃይማኖት መሠረት ጋብቻቸውን

---

[33] ለዚህ ገለፃ ማስረጃው የራሴ ልምድና ከተለያዩ ባለሙያዎች ጋር ከተደረገ ውይይትና የዳሰሳ ጥናት እንዲሁም በክፍል 4 ምልከታ ከሚደረግባቸው ጉዳዮች የተወሰደ ሲሆን ለምሳሌ በአማራ ክልል ለሚታየው ሁኔታ ከአቶ ውብሸት ሽፈራው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ጋር የተደረገ ውይይት ለኦሮሚያ ክልሉ ከአቶ ደረጀ ኢቲቻ ጋር የተደረገ ውይይት ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ከአቶ መርክነህ ይገዙ/ በፍትሕ ሚኒስቴር የሥልጠና መምሪያ ኃላፊ/ጋር የተደረገ ውይይት ተጠቃሾች ናቸው።

[34] Planiol and Ripet, Elementary Treatise on Civil Law. vol. I part 1, p.630

[35] Gosheye Damtew, Effect of Divorce Upon Common Property of Spouses, Ethiopian Civil Service College, Senior Thesis, July 2007) P.19,20 footnotes 56-61 (Unpublished)

[36] ከላይ በቁጥር 11 የተመለከተው ገጽ 228 እና መጽሐፍ ቅዱስ ማቴ. 5÷31 እና ዘዳ 24÷1

ለሚፈጽሙ ተጋቢዎች ተፈፃሚነት ቢኖረው እንጂ ሙሉ በሙሉ በሃገሪቱ የነበረውን የፍቺ አፈፃፀም ሁሉ ይገዛል ለማለት አያስደፍርም:: ምክንያቱም ቢያንስ በ1930ዎቹ በወጡ ሕግጋትና የፍ/ቤት ውሣኔዎች የሲቪል ጋብቻና ባሕላዊ ጋብቻ እውቅና ተሰጥቷቸው ስለነበር በባህልና በፍ/ቤት በተለያዩ ምክንያቶች ፍቺ ይፈፀም እንደነበር ለመረዳት ስለሚቻል ነው::[37] ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ከ1952 ዓ.ም በፊት በነበረው የኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ሕጋዊ ጋብቻ በሃይማኖት እና በሲቪል ጋብቻ ሥርዓት መፈጸም እንደሚቻል በዘመናዊ ሕግ እውቅና ተሰጥቶት እንደነበር በ1922 ዓ.ም የወጣው የዜግነት አዋጅ ድንጋጌዎች ያመለክታሉ::[38] በ1936 ዓ.ም ከወጣው የቃዲዎችና የናኢባዎች ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ለመረዳት እንደሚቻለውም የጋብቻና የመፋታት ሥርዓት በእስልምና ሕግ (ሸሪዓ) መሠረት እንዲፈፀም የሕግ ሥርዓቱ ይፈቅዳል::[39]

በኢትዮጵያ የዳኝነት ታሪክ የከፍተኛው ፍ/ቤት ዳኛ የነበሩት"ናታን ማርይን" የፍትሐብሔር ሕግ ከመውጣቱ በፊት በፃፉት ጽሑፋቸው ከ1952 ዓ.ም የቤተሰብ ሕጉ መውጣት በፊት በኢትዮጵያ ከፍትሐነገሥት በስተቀር ሌላ የጋብቻ ሕግ እንደሌለና ፍ/ቤቶች ጋብቻን የሚመለከት ጉዳይ ሲያጋጥማቸው የሚጠቀሙት በልማድ ሕግ ብቻ እንደነበር ገልፀዋል::[40] ጸሐፊው ስለ ፍቺ የገለፁት፣ ‹‹ልዩ ልዩ የፍቺ ሕግ አለ። የከፍተኛው ፍ/ቤት ዳኞች የሚፈርዱት የሀገር ልማድን ተመርኩዘው ሲሆን አንድ ጉዳይ ሲቀርብላቸው የሚመለከቱት ያንኑ የሚያውቁትንና በየቦታው የሚለያየውን የአገር ልማድ ነው:: ስለዚህ ሕጉ እንደ ባለጉዳዮች የተለያየ መሆን አለበት. . . .››[41] በማለት ነበር:: ከጸሐፊው ገለፃ ለመረዳት እንደሚቻለው ከ1952 ዓ.ም የፍትሐብሔሩ ሕግ መውጣት በፊት ፍቺ የሚፈጸመው በልማድ ሕግ መሠረት በመሆኑ በየቦታው በየብሔርና ብሔረሰቡ የሚለያየውን የአገር ልማድ ተከትሎ እንደነበር ነው። ይህም የፍቺ ሥርዓት ተጋቢዎቹ ያሉበትን ማኀበረሰብ ባህል እና ነባራዊ ሕይወት ከግምት ያስገባ እንደነበር ያመለክታል:: ነገር ግን ፀሐፊው ከፍትሐ ነገሥት በስተቀር ሌላ የጋብቻ ሕግ እንደሌለ የገለጹት ቢያንስ የእስልምና የጋብቻ የሸሪዓ ሕግ እና የሲቪል ጋብቻ ሥርዓት በሕግ እውቅና የተሰጠው ስለነበር አስተያየታቸው የተሟላ መረጃን የፈተሸ ነበር ለማለት አይቻልም::

የፍቺ ክርክር አወሳሰንን በተመለከተ የነበረውን ሥርዓት ለመረዳት እንደሚቻለው ‹‹ስለ ቤተዘመድ የሽምግልና ዳኝነት›› በጥልቀት ጥናት ያደረጉት አቶ አክሊሉ ወልደ አማኑኤል በአዲስ አበባ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከ1939 ዓ.ም እስከ 1948 ዓ.ም ፍርድ የተሰጠባቸውን የፍቺ ክርክር ጉዳዮች ዋቢ አድርገው እንደፃፉት፤ ከ1952 ዓ.ም በፊት የፍቺና ውጤቱ /የንብረት ክፍያና ልጆች አስተዳደግ ጉዳይ/ ባልና ሚስቱ በፈቃዳቸው በሚመርጧቸው ሽማግሌዎች በልማድ ደንብ መሠረት እንዲሁም በአማራጩ በፍ/ቤት ውሣኔ የሚሰጥበት ሁኔታ /ተግባር ነበር::[42] ይህም የሚያስረዳው የፍቺ ውሣኔ ለመስጠት ሁለት አማራጭ መንገዶች እንደነበሩ ነው:: አንደኛው በባልና ሚስቱ ፈቃድ በሽምግልና ዳኝነት ሥርዓት ማስወሰን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ፍቺ ለመወሰን ፍ/ቤ

---

[37] Consolidated Laws of Ethiopia, Ethiopian Nationality Law of 1930, (1972) P. 235-245 እና አክሊሉ ወልደአማኑኤል: ‹‹በ1952ቱ የኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሕግ ውስጥ ያለው የቤተዘመድ ሽምግልና ዳኝነት ስህተትና ጉድለት››፣ የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት 9ኛ ቮልዩም ቁጥር 1 /1965 ዓ.ም/ ገጽ 149 -175

[38] ዝኒ ከማሁ፣ Consolidated Laws (Ethiopia)

[39] በዛኪ. ሙስጠፋ ‹‹በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙት የእስልምና ፍርድ ቤቶች የሚሰራበት ሕግ / ለሸሪዓ ሕግ በሥራ ላይ መዋል መቀጠል ምክንያት የሆኑ ነገሮች›› / የኢት. ሕግ መጽሔት ሾልዩም 9 ቁጥር 1/1965 ዓ.ም/ ገጽ 123፣ በፀሐፊው አዋጅ ቁ. 62/1936 ተጠቅሷል

[40] አክሊሉ ወልደአማኑኤል ከላይ በቁጥር 37 የተመለከተው ገጽ 156

[41] ዝኒ ከማሁ

[42] ዝኒ ከማሁ ገጽ 157-159 በጸሐፊው የተጠቀሱት ፍርዶች በዘውዲቱ ወፈኛ ከሣሽ፣ አልማው ወርቅነህ ተከሣሾች፣ በአዲስ አበባ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የፍ/ብ/መ/ቁ. 347/39 የተወሰነ፣ በዚሁ ፍርድ ቤት በአፀደ ዮሐንስ ከሣሽ፣ ደስታ በላይነህ ተከሣሽ የመ/ቁ. 254/48 /ሁሉም ያልታተሙ/ ናቸው::

ትም ሥልጣን የነበረው መሆኑን ነው:: ይህ በሃገራችን ከ50 ዓመት በፊት የነበረው የፍቺ የሕግ ሥርዓት አሁን ባለንበት ዘመን በዓለማችን በፍጥነት በማደግ ላይ ያሉትን የዲሞክራሲ መርሆዎች፣ የሕግ ዘርፈ ብዙነትን[43] እና አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገዶችን ያካተተ እንደነበር ፍንጭ ይሰጣል:: የፌዴራሉ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 34/5/ የግልና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎቹ ፈቃድ በሃይማኖቶች ወይም በባሕሎች ሕጎች መሠረት መዳኘትን መፍቀዱ: እንዲሁም በክልሎች ሕግጋተ መንግሥት ተዛማጅ ድንጋጌዎች መካተታቸው የዘመናችንን ሥነ- ሕግ እንቅስቃሴ ያገናዘቡ ናቸው::

### 3.4 የፍቺ አፈፃፀም ሥርዓት ከ1952 እስከ 1992 ዓ.ም

ለመጀመሪያ ጊዜ ለቤተሰብ ነክ ጉዳዮች ዘመናዊ ሕግ ሆኖ የታወጀውን የፍትሐብሔሩን የቤተሰብ ሕግ መውጣት ተከትሎ ከሕጉ መታወጅ በፊት ከነበረው የፍቺና ውጤቱ አወሳሰን ሥርዓት ከፍተኛ ልዩነት መፈጠሩን አቶ አክሊሉ ወ/አማኑኤል ከላይ በ ክፍል '3.3' በተጠቀሰው ጥናታዊ ጽሑፋቸው አስምረውበታል::[44] ይኸውም ከሕጉ መውጣት በፊት የፍቺ ጉዳዮች በሁለት መንገዶች ማለትም በባልና ሚስቱ ፈቃድ በሽምግልና ዳኝነት ወይም በፍ/ቤት ውሣኔ ያገኙበት የነበረው ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ተቀይሮ በይግባኝ ካልሆነ በስተቀር የፍ/ቤት ሥልጣን ቀሪ ሆኖ በግዴታ በሽምግልና ዳኝነት ብቻ እንዲታይ መደረጉ ዋነኛው እንደ ችግርም የሚወሰድ መሆኑን ጸሐፊው በዝርዝር ገልፀውታል::[45] ፀሐፊው የሕግ አርቃቂውን ሃሣብ ከአክብሮት ጋር በመተቸት አዲሱን የቤተዘመድ ሽምግልና ዳኝነት ከጥንቱ ጋር ሲያነፃፅሩ፣ «የጥንቱ የሽምግልና ዳኝነት ለህልውናው አስፈላጊ የሆኑትን መሠረታዊ ነገሮች ተገፎና ባዕድ ነገሮችን ተሞልቶ የሚገኘው ያ"የተከበረው የአገር ልማድ"የጥንቱ የሽምግልና ዳኝነት ሥርዓት አሁን ጸንቶ የሚገኘው ቀድሞ በነበረበት አኳኋን ሳይሆን ያልተሟላና የተፋለሰ አቋም ይዞ ነው»፣[46] በማለት ይገልጹታል::

በፍትሐብሔሩ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 727 እንደተደነገገው ከባልና ሚስት ወይም ከሁለቱ አንደኛው ወገን የሚያቀርበው የመፋታት ጥያቄ እንዲወሰን የሚቀርበው ለሽምግልና ዳኞች ነው:: የፍ/ቤት ዳኞች የመፋታት ውሳኔ የተሰጠ መሆን አለመሆኑን አስመልክቶ ክርክር የተነሳ እንደሆን ብቻ ለመዳኘት ሥልጣን ተሰጥቷቸው ነበር::[47]

በፍትሐብሔሩ ሕግ መሠረት ለጋብቻ በፍቺ መፍረስ ከባድና ቀላል የሚባሉ የፍቺ ምክንያቶች ተደንግገው የነበረ ሲሆን ሚስት ባልዋን ወይም ባል ሚስቱን አልፈልግም ማለትንም ሕጉ አይፈቅድም ነበር::[48] ሕጉ በባልና ሚስት ስምምነት የሚደረግ መፋታትንም በሕጋዊ መንገድ ከተፈፀመ እንደሚፈቀድ በአንቀጽ 665/1/ የአማርኛው ንባብ ደንግጎ እንደነበር ይታወሳል:: ፍቺ የሚወስኑት የቤተዘመድ ሽምግልና ዳኞች ብቻ መሆናቸውን፣ ባልና ሚስቱ በፈቃዳቸው እርስበርሳቸው ፍቺ ሊወስኑ እንደማይችሉ የሚገልፁት ዶ/ር ክፍሌ ታደሰ «ይህ ቢፈቀድ ብዙ ትዳር በከንቱ በፈረሰና

---

[42] ዝኒ ከማሁ ገጽ 157-159 በጸሐፊው የተ ጠቀሱት ፍርዶች በዘውዲቱ ወፈኛ ከሣሽ፣ አልማው ወርቅነህ ተከሣሾች፣ በአዲስ አበባ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የፍ/ብ/መ/ቁ. 347/39 የተወሰነ፣ በዚሁ ፍርድ ቤት በአፀደ ዮሐንስ ከሣሽ፣ ደስታ በላይነህ ተከሣሽ የመ/ቁ. 254/48 /ሁሉም ያልታተሙ/ ናቸው::

[43] Alemayehu Fentaw, “Legal Pluralism; Its Promises and pitfalls for Ethiopia”, Jimma University Journal of law, Vol. I No. 1, October 2007, p.35-66 and Andre J. Hoekema (Amsterdam University Professor), Aspects of Legal Pluralism in the Federal set up of Ethiopian state, in : Ethiopian Journal of Development Research (Institute of Development Research), (Addis Ababa) Vol.24 No. 2, October 20002. P.1-39

[44] አቶ አክሊሉ ወ/አማኑኤል ከላይ በቁጥር 37 የተመለከተው

[45] ዝኒ ከማሁ ገጽ 160-161

[46] ዝኒ ከማሁ

[47] የፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 729

[48] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 664 እና 667 - 670

ልጆችም ሜዳ በቀሩ ነበር»፤[49] በማለት ይደመድማሉ:: ለፀሐፊው ሃሳብ አክብሮቴን እየገለፅኩ በመደምደሚያው ግን በከፊል አልስማማም:: ምክንያቱም ጋብቻ የተጋቢዎቹ የግል ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን ፍቺስ ቢያንስ በከፊል ለምን የእነሱ ጉዳይ አይሆንም? ባለንበት የህብረተሰብ ተሳትፎ ወሳኝ በሆነበት የዲሞክራሲ ግንባታ ሥርዓት ዘመን ፍቺ የመወሰኑ ሥልጣን የፍ/ቤት ብቻ መሆኑና ለተጋቢዎቹ ሥልጣን ቅድሚያ አለመስጠቱ ውጤታማ ነውን? አንድ የዩንቨርስቲ የሕግ ምሁር በአግራሞት እንደሚያሰምሩበት #ለጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት ሦስት መንገዶች/በሮች ተፈቅደውለት እያለ ለፍቺ ሥርዓቱስ ለምንድነው አንድና አንድ መንገድ ብቻ/ ማለትም በፍ/ቤት ውሳኔ ብቻ እንዲከናወን የሚደረገው?;[50] ያሉት በዚህ ረገድ አወያይ ጭብጦችን ያስነሳል:::: ለእነዚህ ጭብጦች ምላሽ ለመስጠት ቀጥሎ የሚቀርቡትን የጽሑፉን ክፍሎች መመልከቱ የተሻለ ይሆናል::

### 3.5 የፍቺ አፈፃፀም ሥርዓት በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ፍቺ ስለሚወሰንበት ሥርዓት በአንቀጽ 76 የሚከተለውን ያስነብባል፤

ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ ሊወሰን የሚችለው:-

ሀ. ባልና ሚስት በስምምነት ለመፋታት ሲወስኑና ይህንኑ በፍርድ ቤት አቅርበው ውሳኔያቸው ተቀባይነትን ሲያገኝ ወይም

ለ. ከተጋቢዎቹ አንዱ ወይም ሁለቱ ተጋቢዎች በአንድነት ጋብቻቸው በፍቺ እንዲፈርስ በፍርድ ቤት ጥያቄ ሲያቀርቡ ነው::

ከዚህ ድንጋጌ ግልጽ ንባብ ለመረዳት እንደሚቻለው ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ የሚወሰነው በሁለት መንገዶችና በሁለት አካላት ነው:: የመጀመሪያው በባልና ሚስቱ በስምምነት ለመፋታት በራሳቸው ሥልጣን በሚደረግ ውሳኔ ነው:: ይህ የባልና ሚስቱ የፍቺ ውሳኔ በፍ/ቤት ቀርቦ ተቀባይነትን የማግኘትና የመጽደቅ ፎርማሊቲ እንደሚያስፈልገውም ተመልክቷል:: ባልና ሚስቱ በፍ/ቤት በሚያቀርቡት የፍቺ ስምምነት ላይ ለመፋታት የወሰኑበትን ምክንያት እንዲገልፁ እንዳይገደዱም ሕጉ ነፃነትን ሰጥቷቸዋል::[51] በሌላ በኩል ደግሞ ሕጉ ክርክሮችን ስለመወሰንና ስለፍ/ቤት ሥልጣን በሚናገረው ምዕራፍ ሥር በአንቀጽ 117 ፍቺን የመወሰን ወይም የፍቺ ውጤቶችን በተመለከተ ውሳኔ የመስጠት ወይም የማጽደቅ ሥልጣን የፍ/ቤት ብቻ መሆኑን ያውጃል:: በቀዳሚው አንቀጽ ባልና ሚስቱ በስምምነት ፍቺን መወሰን እንዲችሉ ሥልጣን ሰጥቶ ለፍ/ቤቱ የማጽደቅን ሚና ብቻ ከሰጠ በኋላ ስለ ፍ/ቤት ሥልጣን በደነገገበት ክፍል ደግሞ ፍቺን የመወሰን ሥልጣን የፍ/ቤት ብቻ ነው ማለቱ በአንቀጾቹ መካከል ልዩነትን ፈጥሯል::

ሁለተኛው ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ ሊወሰን የሚችልበት መንገድ በአንደኛቸው ወይም በሁለቱም ተጋቢዎች በሚቀርብ ጥያቄ መሠረት ጋብቻው በፍቺ ሲወሰን ነው:: በዚህ የፍቺ አፈፃፀም ሥርዓት መሠረት ባልና ሚስት ያላቸው ሚና በፍ/ቤት አቤቱታ ማቅ ረብ ሲሆን ለፍ/ቤቱ ደግሞ ፍቺውን የመወሰን ሥልጣን ተሰጥቶታል::

ፍቺን የመወሰን ወይም የፍቺ ውጤቶችን በተመለከተ ውሳኔ የመስጠት ወይም የማጽደቅ ሥልጣን የፍ/ቤት ብቻ እንዲሆን የታወጀው በፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ ብቻ ሳይሆን በክልሎች የቤተሰብ ሕግጋትም ጭምር ነው:: በዚሁ መሠረት በትግራይ ብሔ

---

[49] ክፍሌ ታደሰ (ዶ/ር) በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ የቤተሰብ ሕግ፣ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ 1990፣ ገጽ 106

[50] ይህ አገላለጽ የተወሰደው ከአቶ ኤልያስ ኑር የቅድስት ማርያም ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ሕግ ፋኩልቲ ዲን ጋር ከተደረገ ውይይት መሆኑን ለመጥቀስ እወዳለሁ::

[51] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 77/3/

*ራዊ ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 97፣[52] በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 128፣[53] በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቤተ ሰብ ሕግ አንቀጽ 98፣[54] በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 132፣[55] በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 141፣[56] እንዲሁም በጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ረቂቅ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 121፣[57] ፍቺና ውጤቱን የመወሰን ሥልጣኑ በሁሉም የቤተሰብ ሕጐች ለፍ/ቤት ብቻ እንዲሆን ተደርጓል፡፡*

*ከላይ በዝርዝር እንደተመለከተው በሁለቱም የፍቺ አፈፃፀም መንገዶች ስለፍቺና ውጤቱ የመጨረሻውን ይሁንታ የመዳኘት ሥልጣን የተሰጠው ለፍ/ቤት ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የተፈቀደው የፍቺ አፈፃፀም ሥርዓቱ ሁለት ቢመስልም ከውጤቱ አንፃር ግን አንድ መንገድ ብቻ መሆኑን ለመደምደም ይቻላል፡፡ ይኸውም ሁኔታ በባልና ሚስቱ ፈቃድ/ምርጫ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በግዴታ የተደነገገ ደንብ ነው፡፡ በቤተሰብ ሕግጋቱ በፍቺ አፈፃፀም ሥርዓት ላይ የተወሰደው አቋም በሕገ መንግስቱ የተፈቀደውን በባህል ሕጐች መሠረት የመዳኘትን መብት እና አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገዶችን የመጠቀምንም በር የዘጋ ነው ቢባል ስህተት ያለው ሃሳብ አይሆንም፡፡*

*ኢትዮጵያ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ያሉባት ሀገር መሆኗ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም በፌዴራሉም ሆነ በክልሎች ሕግጋተ መንግስት በተመሳሳይ ሁኔታ ማንኛ ውም ብሔር ብሔረሰብ ሕዝብ ባህሉን የመግለጽ፣ የማዳበርና የማስፋፋት እንዲሁም ታሪኩን የመንከባከብ መብት ተሰጥቶታል፡፡[58] ባህል ከሚገለጽበት፣ ከሚዳብርበትና ከሚስፋፋበት አንዱና ዋነኛው ማህበራዊ ገጽታው ደግሞ የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብቶችን የሚመለከተው ሥርዓት ነው፡፡ በመሆኑም በሃይማኖቶችና በባህል ሥርዓት ለሚፈፀሙ ጋብቻዎች ሕገ መንግስትዊ እውቅና ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም ሕገ መንግስቱ የግል እና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሃይማኖቶች ወይም በባህሎች ሕጐች መሠረት መዳኘትን በመፍቀዱ የባህልና የሃይማኖት ፍ/ቤቶች ሊቋቋሙ እንዲችሉም ፈቃጅ ድንጋጌ አካትቷል፡፡[59] ለዚህም በምሳሌነት በሸሪዓ ፍ/ቤት በባልና ሚስቱ ፈቃድ የጋብቻና ፍቺን ጉዳይ ለመዳኘት በሕግ የተሰጠውን ሥልጣን መጥቀሱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡[60]*

*በሀገራችን የሕግ ሥርዓት ለ40 አመታት ገዥ ሆኖ በቆየው የቤተሰብ ሕግ ለፍቺ ምክንያት በሚጠየቅበት፣ ፍቺ እንደ መብት በማይታይበትና ውስብስብ ክርክር በሚያስነሳበት ሥርዓተ ሕግ ዘመን ፍቺና ውጤቱን በተመለከተ ዳኝነት የመስጠቱ ሥልጣን ለቤተዘመድ ጉባኤ በምሉእነት ተሰጥቶ በነበረበት ሁኔታ ሌላውን ጫፍ/ፅንፍ በመያዝ በአዲሱ የቤተሰብ ሕግ ከላይ የተገለጹት ለፍቺ ምክንያት የመጠየቅና ሌሎቹም*

---

[52] የተሻሻለው የትግራይ ብሔራዊ ክልል መንግሥት የቤተሰብ ሕግ፣ አዋጅ ቁጥር 116/99/በ1991 ዓ.ም. የወጣውን እንዳሻሻለው፣ አንቀጽ 97/1/

[53] የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት የቤተሰብ ሕግ፣ አዋጅ ቁጥር 79/1995፣ ዝክረ ሕግ 8ኛ ዓመት ቁጥር 3፣ አንቀጽ 128

[54] የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቤተ ሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 69/95 / በአዋጅ ቁጥር 83/96 እንደተሻሻለ/ *መገለተ ኦሮሚያ*፣ አንቀጽ 98

[55] የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልል መንግሥት የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 75/1996 በተለይ የወጣ ደቡብ *ነጋሪት ጋዜጣ* ፣አንቀጽ 132

[56] የተሻሻለው የቤንሻንጉል ጉመዝ ክልላዊ መንግሥት የቤተሰብ ሕግ፣ አዋጅ ቁጥር 63/1998 ፣ አንቀጽ 141

[57] የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ረቂቅ የቤተሰብ ሕግ፣ 1999 ዓ.ም አንቀጽ 121

[58] የፌዴራል ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 ፤ የክልሎች ሕግጋተ መንግሥት ተዛማጅ አንቀፆችም ተመሳሳይ ድንጋጌ ይዘዋል

[59] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 34/5/ እና አንቀጽ 78

[60] የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር የወጣ አዋጅ፣ 1992 ዓ.ም ቁጥር 188 *ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ* ፣6ኛ አመት ቁጥር 10

ነገሮች ተቃራኒ በሆነበት ሁኔታ ዳኝነቱ በአስገዳጅነት ለፍ/ቤት ብቻ መሰጠቱ ለምን? የሚል ክርክር የሚያስነሳ ነው፡፡ ይህ ጭብጥ በተለይም ከ80% በላይ ከሆነው የገጠራቱ ኢትዮጵያ ነዋሪ ነባራዊ የጋብቻና ፍቺ ሕይወት/ሥርዓት አፈፃፀም አንፃር ሲታይ የሕጉን ምክንያታዊነትና ሃገራዊነት አከራካሪ ያደርገዋል፡፡[61] ለፍቺና ውጤቱ ክርክሮች ሂደትና አወሳሰኑ እንደመሠረታዊ ችግርም የሚቆጠረው አንዱ ይኸው ሁኔታ ከፍ/ቤት ውሳኔ በስተቀር ፍቺ የለም ብሎ የሚደመድመው አማራጮችን የዘጋው የሕግ አቋም ነው ለማለት ይቻላል፡፡ በዚህ ረገድ የፀሐፊው ፍላጐት ከሃገራችን ነባራዊ የማኅበረሰቡ የጋብቻና ፍቺ እውነታ /Social realities / አንፃር ለምን ሥልጣኑ በፍርድ ቤት ብቻ ይገደባል? አማራጭ መንገዶች እና ማህበራዊ እውነታዎች ለምን የሕግ እውቅና አይሰጣቸውም? ሕጉ የማህበረሰቡን እውነታ ሊያንፀባርቅ አይገባውም ወይ? ባልና ሚስት ተለያይተው፣ በየፊናቸው ትዳር መሥርተውና ከሌላ ትዳር ልጆች ወልደው፣ አንዱ ሲሞት ከሟች ጋር የነበረኝ ትዳር በፍ/ቤት ስላልፈረሰ የሟች ሚስትነት/ባልነት ይረጋገጥልኝ የሚል ጥያቄ ማቅረብ ከሕጉ መንፈስና ዓላማ (purpose and function) አቋም ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል ወይ? በሚሉ ጭብጦች ላይ ትንተና ማድረግ ነው፡፡

ከእነዚህ ነጥቦች ጋር በተያያዘ መልኩ ፍቺና ውጤቱን የመወሰን ሥልጣኑ ለፍ/ቤት ብቻ የመገደቡን አግባብነት በጥልቀት ለመፈተሽ ይረዳ ዘንድ በመደበኛ ፍ/ቤቶች ፍቺና ውጤቱን ለማስወሰን የገጠሩ ነዋሪ ልማዶችና ግንዛቤስ የቱን ያህል የዳበረ ነው? ፍ/ቤቶች በቦታና በጊዜ በቀላሉ ተደራሽ ናቸውን? በፍ/ቤት ተሟጋች በመሆንስ ጉዳይ የህበረተሰቡ አመለካከትስ ምን ይመስላል? ከሕጉ ሃሳብ ጋር ይሄዳል? ሕጉ እየተፈፀመ ነው? ባለመፈፀሙስ ተጐጂ ዜጐች የሉምን? የሚሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች ማንሳቱ ለችግሩ መፍትሔ ለመሻት ጠቃሚ ነው፡፡ በእርግጥ እነዚህን ጭብጦች እያንዳንዳቸውን በዝርዝር ለመተንተን የፅሑፉ መጠነ ይዘት አይፈቅድም፡፡ ጥያቄዎቹ መነሳታቸው በራሱ ግን ወደ መልሱ ይመራናል፡፡ የሚቀጥለው ክፍል በፍ/ቤቶች ውሳኔ በተሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ የሚደረገው መጠነኛ ጥናትና ምልከታ ተደርጓል፡፡

## 4. በፍ/ቤቶች ውሳኔዎች ላይ የተደረገ ምልከታ፣

የሕግ መሠረታዊ ዓላማው የሰዎችን ኢካኖሚያዊ ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ዘርፈ ብዙ ግንኙነቶችን በሥርዓት መጠበቅ፣ መምራት እና አለመግባባቶችን በመፍታት መሠረታዊና ሕገመንግስታዊ መብቶችና ነፃነቶችን ማስከበር መሆኑን በዓለማችን ህብረተሰብ ተቀባይነትን ያገኘ መርህ ነው፡፡ ሕግ ይህንን ዓላማና ግቡን ለማሳካት የሚችለውም በሕግ አውጭው ከማህበረሰቡ ነባራዊ ሕይወት ጋር ተገናዝቦና ተፈፃሚነቱም ከግምት ገብቶ መውጣት ሲችል እና በሕግ ተርጓሚ አካላቱ በአግባቡ መተርጐም/መተግበር ሲችል መሆኑም ግልጽ ነው፡፡

የሕግ አተረጓጐም ተግባር የሕግ ትርጉም አስፈላጊ ስለሚሆንበት ጊዜ አምስት ዓለም አቀፍ ተቀባይነትን ያገኙ መሠረታዊ መርሆች ስለመኖራቸው በፕሮፌሰር ጆርጅ ክስቼኖቪች «በአዋጅ የወጣ ሕግ ትርጉም በኢትዮጵያ» በሚለው ጹሑፋቸው ማብራሪያ የሰጡበት ይጠቀሳል፡፡[62] እነዚህም ሕጉ ግልፅ በሆነበት ጊዜ ትርጉም አስፈላጊ አይሆንም በአንፃሩ ደግሞ፣ ትርጉም አስፈላጊ የሚሆነው ሕጉ የሚያሻማ በሚሆንበት ላይ፣ ሕጉ ባረመመበት/በማይናገርበት/፣ ሕጉ እርስበርሱ ተፃርሮ በሚፋለስበትና በሚያሻማበት እና

[61] በተለይም በክልሎች ወደ ፍ/ቤት መሄድ ሳያስፈልግ በአካባቢ / ባህል ሽምግልና ዳኝነት ሰማንያ ወይም የጋብቻ ውል በመቅደድ ወይም በተጋቢዎች ድርጊታዊ /የቃል ስምምነት መለያየትና ጋብቻን በእውነተኛ / ዲፋክቶ/ ማፍረስ የተለመደ ነው፡፡ ለማስረጃ ማጣቀሻነት ከላይ በቁጥር 33 የተጠቀሰውን ይመልከቱ፡፡

[62] ጆርጅ ክሽኖቭች /ፕሮፌሰር/ "በኢትዮጵያ ውስጥ የሕግ አተርጓጎም" የኢት. ሕግ መጽሄት 1ኛ ቮልዩም ቁጥር 2 /1957 ዓ.ም፣ ገጽ 299-314.

በመጨረሻም ሕጉ ከአእምሮ ሚዛን ውጭ በሆነበት ወይም የነጠላ ንባቡ ውጤት ኢ-ምክንያታዊ በሆነበት ጊዜ ነው::[63]

ኒል ማክ ኮርሚክ /Neil MacCormick/ ሕግ ሲተረጐም ወይም በሥራ ላይ ሲውል ወጥነት ያለው፣ ከሕግ ሥርዓቱ ጋር  የሚስማማ መሆን እና የትርጉሙ ውጤት / Consisteney, coherence and consequence/ ሁልጊዜ ከግምት መግባት እንዳለባቸው ያሳስባል::[64] ይህም የሕግ አተረጓጐም ተግባር ወጥነት ያለው፣ ከሕግ ሥርዓቱ ጋር የሚስማማና ውጤታማ ይሆን ዘንድ ልዩ ጥንቃቄ፣ እውቀትንና ክህሎትን የሚጠይቅ መሆኑን ያስገነዝባል::

በፍ/ቤቶች የሚሰጡ የሕግ ትርጉሞች የተወሳሰቡ የፍሬ ነገር፣ የማስረጃና የሕግ ክርክሮችን መሠረት ያደረጉ፣ እንዲሁም ረቺና ተረቺ ያለባቸው በመሆናቸው እና ከተከራካሪ ወገኖችም ሆነ ከሕግ ማህበረሰቡ ትችትን የሚያስከትሉ በመሆኑ ምርምርና ጥንቃቄ የተመላበት ትንተና ይሻሉ:: በፍ/ቤቶች የሚታዩት የሕግ አተረጓጐም አቋሞች በዜጎች ሕይወት፣ ንብረትና ሌሎች ሕገ መንግስታዊ መብቶችና ነፃነቶች ላይ ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤቶች ያላቸው ናቸው:: ይህንን አጠቃላይ የመነሻ ሃሳብ መሠረት በማድረግ "ሳይፋቱ" /ዲፋክቶ/ ፍቺን በተመለከተ በፌዴራል ፍ/ቤቶችና በሁለት ክልሎች ፍርዶች የታዩት መሠረታዊ ልዩነት የሚታይባቸው የሕግ አተረጓጐም ፈለጐች እንደሚከተለው ቀርበዋል::

### 4.1 ፍርዶች ላይ የተደረገ ምልከታ

ብዙዎቹ ፍርዶች ከፌዴራል ፍ/ቤቶች የተወሰዱ ሲሆኑ ከክልሎች ፍ/ቤቶችም ለአብነት የተወሰዱ ፍርዶች ተካተዋል::  ይሁንና ፍርዶቹ በሌሎችም ክልሎች ለሚታዩ የውሳኔ አሰጣጥ ልዩነቶች እንደ ምሳሌ የሚወሰዱ እንጂ አብነታቸው ውሳኔዎቹን ለሰጡት ፍ/ቤቶች ብቻ አይደለም:: የምልከታውን አቀራረብ ቅደም ተከተል በውሣኔዎቹ ተመሣሣይነት ዘርፍ ከፋፍሎ ከማቅረብ ይልቅ እንደ አግባብነቱ በአንድ ጉዳይ ላይ የሚታዩትን የተለያዩ ፍ/ቤቶች አተረጓጐም በማሳየት ላይ የተመሠረተ ነው::

#### 4.1.1. <u>መ/ቁ 75912</u>

አመልካቾች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 75912[65] በጋራ መስከረም 22 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ በ1956 ዓ.ም ጋብቻ ፈጽመው ባልና ሚስት እንደነበሩና ከ1961 ዓ.ም ጀምሮ ተለያይተው እንደሚኖሩ ንብረታቸውንም በተለያዩበት ጊዜ መከፋፈላቸውን በመግለጽ የስምምነት ፍቺ ፀድቆ ማስረጃ እንዲሰጣቸው አመልክተው በማስረጃነትም መስከረም 14 ቀን 1999 ዓ.ም የተደረገ የፍቺ ስምምነት አቅርበዋል:: ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ፤

> "ጋብቻ ሕጋዊ ድርጊት እንደመሆኑ መጠን ሕጋዊ ውጤትም የሚኖረው ስለመሆኑ የታወቀ ነው:: እነዚህም ሕጋዊ ውጤቶች በተጋቢዎቹ ግላዊ ግንኙነት ወይም በተጋቢዎቹ የንብረት ግንኙነት ላይ ወይም በሁለቱም ላይ ተጽዕኖ የሚኖራቸው ናቸው:: . . . በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ድንጋጌ አንፃር መከባበርና መደጋገፍ፣ የቤተሰብ የጋራ አመራር መስጠት፣ አብሮ የመኖር ግዴታ እና የመተማመን ግዴታ እንዳለባቸው  ተደንግጓል:: ከዚህ ድንጋጌ አኳያ የግራ ቀኙ የጋብቻ ሁኔታ ሲፈተሽ

---

[63] ዝኒ ከማሁ

[64] Neil MacCorrmick, <u>The Artificial Reason and Judgment of Law</u>, 1992, p.167-182. Vol.1 (Amsterdam University and Ethiopian Ministry of Justice joint LL.M programme reference material )

[65] አመልካቾች ዘውዴ  አስፋውና ወ/ሮ ካሰች ወልደየስ /ተጠሪ የለውም/፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት፣ የመ/ቁ 75912/ መስከረም 23 ቀን 1999 ዓ.ም /ያልታተመ/ /ከዚህ በኋላ በዚህ ጽሁፍ ክፍል መጀመሪያ ደረጃ፣ ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍ/ቤት የሚለው የፌዴራሉን ፍ/ቤቶች መሆኑን ልብ ይሏል::/

> *ግንኙነታቸው የተቋረጠው ከታህሣስ 27 ቀን 1961 ዓ.ም ጀምሮ ስለሆነና በማህበራዊም ሆነ በግላዊ ግንኙነታቸው ላይ የሚያስከትለው ውጤት የተቋረጠ ከመሆኑም በተጨማሪ ጋብቻው የቀረ በመሆኑ አመልካቾች ከ38 ዓመታት ቆይታ በኋላ ጋብቻው በሕይወት እንዳለ በማስመሰል ያደረጉትን የፍቺ ስምምነት ፍ/ቤቱ ውድቅ አድርጐታል።"*

በማለት የፍቺውን ጥያቄ ባለመቀበል ውሣኔ ሰጥቷል።

በዚህ ውሣኔ ላይ በአመልካቾች አማካኝነት ይግባኝ የቀረበለት የከፍተኛው ፍ/ቤት ደግሞ ጉዳዩን አይቶ ጋብቻ የሚፈርስባቸውን ምክንያቶች በአንቀፅ 75 የተመለከቱትን በመጥቀስ፣ "ምንም እንኳን ይግባኝ ባዮዎች የተለያዩት በ1961 ዓ.ም እንደሆነ የተገለጸ ቢሆንም በፍ/ቤት ፍቺ አስወስነው የተለያዩ ባለመሆኑ ያቀረቡትን የፍቺ ጥያቄ የሥር ፍ/ቤት ያልተቀበለው አላግባብ ነው፤[66] "በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ከተቸ በኋላ የፍቺ ስምምነቱን ተቀብሎ በማፅድቅ ውሣኔ ሰጥቷል።

እነዚህ የሁለቱ ደረጃዎች ፍ/ቤቶች ውሣኔዎች መሠረታዊ ልዩነት ያላቸው የሕግ አተ ረጓጐም የታዩባቸው ናቸው። የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ ጋብቻ ከውጤቱ ጋር ሆኖ በሕይወት ካልተገኘና ተጋቢዎች ለረጅም ጊዜያት ተለያይተው ከኖሩ፣ ውጤቱ ቀሪ የሆነን ጋብቻ ፍርድ ቤት በፍቺ እንዲፈርስ ሊወሰን አይገባውም የሚል አተረጓጐም ሲሆን የይግባኝ ሰሚው የከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ ተጋቢዎች ለ38 ዓመታት ተለያይተው ቢኖሩም፣ እናም የጋብቻ ግላዊ ግንኙነት ውጤት ተቋርጦ የነበረ ቢሆንም፣ ጋብቻቸው በፍ/ቤት ውሣኔ እስካልፈረሰ ድረስ የፍቺ ውሣኔ ሊሰጥት ይገባል የሚል ነው።

#### 4.1.2. <u>መ/ቁ 91430</u>

በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 91430[67] የተወሰነ ሌላ የፍቺ ጉዳይ እንደሚያስረዳው አመልካቾች በ1961 ዓ.ም ጋብቻ ፈጽመው ባልና ሚስት እንደነበሩ ከ1966 ዓ.ም ጀምሮ ተለያይተው በየግላቸው ትዳር መመስረታቸውን ገልጸው ልጃቸው ጋር አሜሪካ ለመሄድ ፍቺውን መፈለጋቸውን በማመልከት ፍቺ ተወስኖ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል። ጉዳዩ የቀረበለት ችሎት፣

> "ጋብቻው ነበር ለማለት ካለመቻሉም በላይ ግራ ቀኙም ከተለያዩ በርካታ ዘመናትን ያስቆጠሩ ከመሆኑም በተጨማሪ ፍቺ ደግሞ በግራ ቀኙ መካከል የነበ ረው ትስስር የሚቋረጥበት ሁኔታ እንደመሆኑ መጠን ግራ ቀኙ ያቀረቡት የስምምነት ፍቺ ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ነው፤"

በማለት አቤቱታውን ዘግቶታል።

የዚህ ውሣኔ ሕግ አተረጓጐም ጋብቻን ከትርጉሙና ከውጤቱ ጋር አገናኝቶ እንጂ በአንድ ወቅት የተፈፀመ ጋብቻ በፍ/ቤት የፍቺ ውሣኔ አልተሰጠበትም በሚል ምክንያት ብቻ ጋብቻው እንደቀጠለ መቆጠር የለበትም የሚል መነሻ (premise) እንዳለው እንረዳለን።

#### 4.1.3 <u>መ/ቁ 80/76</u>

ከላይ በቁጥር 4.1.2 ከተጠቀሰው ጉዳይ ጋር ተመሣሣይ ጭብጥ በነበረው በፍትሐብሔሩ የቤተሰብ ሕግ አተረጓጐም ተመሣሣይ የትርጉም ልዩነት እንደነበር

---

[66] ይግባኝ ባይዎች አቶ ዘውዱ አስፋውና ወ/ሮ ካሰች ወልደየስ / መልስ ሰጭ የለውም/ /የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የቤተሰብ ጉዳዮች ይግባኝ ችሎት፣ የመ/ቁ. 49631፣ /ጥቅምት 24 ቀን 1999 ዓ.ም/ /ያልታተመ/

[67] አመልካቾች አቶ ገመቹ ሽቦ እና ወ/ሮ ስህን አየለ /ተጠሪ የለውም/፣ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ የመ/ቁ. 91430/ በ 26/10/99 ዓ.ም/ /ያልታተመ/

በቀድሞው ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 80/76 በድምፅ ብልጫ የተሰጠ ፍርድ ያረጋግጣል።[68] በዚህ ጉዳይ ባልና ሚስቱ ያለ ፍቺ ውሣኔ ለ12 ዓመታት ተለያይተው ባል ከሌላ ሴት ጋር በጋብቻ፣ ሚስት ደግሞ ከሌላ ወንድ ጋር ከጋብቻ ውጭ እንደ ባልና ሚስት በመኖር ላይ እያሉ ባል ሲሞት የቀድሞዋና የኋለኛዋ ሚስቶች ሚስትነት እንዲረጋገጥላቸው በማመልከት ሙግት ይገጥማሉ። የከፍተኛው ፍ/ቤት የቀድሞው ጋብቻ በባልና ሚስቱ እውነተኛ መለያየተና ከሌላ ሰው ጋር በጀመሩት ግንኙነት በእውነታ መፍረሱን በመግለጽ የኋለኛዋ ሚስት ብቻ የሟች ሚስት ነች በማለት ወስኗል። ይግባኝ የቀረበለት ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ደግሞ ጋብቻ የሚቋቋምበት ሥርዓት እንዳለው ሁሉ የሚፈርስበት ሥርዓትም ያለው መሆኑን በመመዝገብ ባልና ሚስቱ ለረጅም ጊዜ መለያየታቸውና ከሌላ ሰው ጋር ግንኙነት መመሥረታቸውም ቢሆን የቀድሞውን ጋብቻ አያፈርሰውም በማለት «ሁለቱም ሴቶች የሟች ሚስቶች ናቸው» በማለት ፍርድ ሰጥቷል።

በአንፃሩ ደግሞ ከአብላጫው ውሣኔ በሃሳብ የተለዩት ዳኛ[69] የሰጡት የልዩነት ሃሳብ የሚከተለው ነበር

> #...ሁኔታው እንዲህ ግልፅ ከሆነ ይግባኝ ባይዋ ከአሥር አለቃ በቀለ ጋር ለመፋታታቸው የፍች ውሳኔ ካልቀረበ ጋብቻው እንዳልፈረሰ ይቆጠራል የሚለውን መሠረተ ሃሳብ አልስማማበትም። በመሠረቱ በኢትዮጵያ በአብዛኛዎች ክፍላተ ሃገር በጋብቻ ጊዜ እንደሚደረገው ሥነ ሥርዓት በፍች ጊዜ ሊፈጽም አይችልም። በፍች ጊዜ ሽምግልና ጉባዔ ተቋቋመም አልተቋቋመም የጋብቻውን መፍረስ ሁለቱ ወገኖች አምነውና ወደው ተቀብለው ወንድየው ሌላ ሚስት ሴቲቱ ሌላ ወንድ አግብተው 2 ወይም ከዚህ በላይ ልጆች ወልደው ሲኖሩ ቆይተው በመጨረሻ አንዱ ከሌላው ጋር የነበረኝ ጋብቻ ሕጉ በሚያዘው መሠረት ሽምግልና ጉባዔ ተቋቁሞ የተወሰነ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ እስካልቀረበ ጋብቻው ፀንቶ እንደቆየ ይገመትልን የሚሉ ወገኖችን ጥያቄ መቀበል በእኔ አስተያየት አደገኛ ሆኖ ይታየኛል;።

ይህንኑ የቀድሞውን የቤተሰብ ሕግ መሠረት አድርጐ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአንድ የወንጀል ጉዳይ «በጋብቻ ላይ ጋብቻ ተፈጽሟል» በሚል ክስ በቀረበለት ጉዳይ ተከሣሹን በ6 ወር እስራት ከቀጣው በኋላ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተከሣሹ የቀረበውን ይግባኝ መርምሮ ይግባኝ ባዩ ከቀድሞዋ ሚስቱ ጋር ፍቺ ባይፈጽሙም በሽምግልና ውሣኔ ፣ መለያየታቸውን እንደ ፍቺ በመቁጠር ተከሣሹን ከወንጀሉ ክስ በነፃ ያሰናበተበት ውሣኔም ከላይ ከተመለከተው የልዩነት ሃሣብ ጋር የሚስማማ ትርጉም ነው።[70]

በእነዚህ በቀድሞውም የቤተሰብ ሕግ መሠረት በተሰጡት ውሣኔዎች መካከል የታዩት የሕግ አተረጓጐም ልዩነቶች፤ "ሳይፋቱ" (ዲፋክቶ) ፍቺን የሚመለከቱ ጉዳዮች አወሳሰን ፍቺ በሽምግልና ዳኝነት በሚወሰንበት የቀድሞው ሕግ ሥርዓትም ወቅት የነበረ ችግር መሆኑን ያመለክታሉ። ይህም ሁኔታ ችግሩ በቀድሞው ሕግ የነበረና መፍትሔ የሚሻም ሆኖ እያለ የተሻሻለው ሕግ ሲወጣ ያላየውና እልባት ያልሰጠበት፤ አብሮ የመኖር

---

[68] Melesse Damte (Assistant Professor), Divorce under the Ethiopian Legal System: an over view /፣ በ1994 ዓ.ም ለፌዴራል ዳኞች ለሥልጠና የቀረበ/ ገጽ 20-21 በጽሑፉ የተመዘገበው የፍ/ቤት ጉዳይ፤ ይግባኝ ባይ ወ/ሮ ብሪቱ ገርባ ፤ መልስ ሰጭ ወ/ሮ አበበች አንገሬ፣ የቀድሞው ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት፣ የመ/ቁ 80/76 / ያልታተመ/

[69] ዝኒ ከማሁ

[70] ዝኒ ከማሁ ገጽ 21፣ ከሣሽ /መልስ ሰጭ/ ዐቃቤ ሕግ ተከሣሽ /ይግባኝ ባይ/ አቶ ስጦታው ታፈሰ፣ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ፣ የወ.መ.ቁ 571/88 /ያልታተመ/።

ግጼታን አለመወጣት ወይም መለያየት ምን ውጤት እንደሚኖረው የተደነገ አለመሆኑ የሕግ ክፍተት መኖሩን ያመለክታል፡፡

### 4.1.4 የመ/ቁጥር 72399

በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች (ባል) እና ተጠሪ (ሚስት) በ1998 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ ከተጠሪ ጋር በአገር ባሕል ልማድ ሐምሌ 23 ቀን 1953 ዓ.ም ጋብቻ ፈጽመው ለአንድ ዓመት አብረው ከኖሩ በኋላ ሰኔ 14 ቀን 1954 ዓ.ም ተለያይተው ከ40 ዓመት በላይ አብረው አለመኖራቸውን፣ መለያየቱ ማለትም ፍቺው በሁለታቸው ፈቃድ ከተ ፈጸመ በኋላ ተጠሪዋ አሜሪካን አገር ሄደው የሚኖሩ መሆኑን በመግለጽ የፍቺ ውሣኔ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡[71] ተጠሪም በወኪላቸው አማካኝነት በፍቺው ጥያቄ ተስማምተ ውበታል፡፡

ፍ/ቤቱ "በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተፈጽሟል የሚባለው ጋብቻ በሕይወት አለ ወይስ የለም?" የሚል ጭብጥ መሥርቶ "ጋብቻው ያስከተለው ግላዊም ሆነ የንብረት ውጤት ባለመኖሩና ጋብቻው ከተቋረጠ ከ40 ዓመት በላይ ያስቆጠረ በመሆኑ እንዲሁም መለያየቱ በሁለቱ ፈቃድ ተፈፅመ የሚለው ፍቺ ተፈጽሞ እንደነበር ስለሚያመለክት የቀረበውን የፍቺ ጥያቄ አልተቀበልኩትም" በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሣኔ ፍ/ቤቱ ስለመለያየትና ፍቺ የሰጠው የሕግ ትርጉም ተጋቢዎቹ በፈቃዳቸውና በስምምነት የጋብቻ ትስስራቸውን አቋርጠው ተለያይተው ከኖሩ እንደተ ፋቱ መቆጠር አለበት የሚል፤ ተጋቢዎቹ ያለ ጥብቅ ፎርማሊቲ ለመፋታት ነፃነት ይሰጣቸው የሚለውን አስተሳሰብ የሚደግፍ ነው፡፡ አቋሙ በእውነታው /በተግባር ጋብቻ ቸውን ያፈረሱ ተጋቢዎች ጋብቻቸው አስቀድሞ በመፍረሱ በፍ/ቤት ይፍረስ ተብሎ መወሰን አይገባውም የሚል ከመሆኑም አንፃር "ሳይፋቱ" /ዲ ፋክቶ/ ፍቺን እውቅና የሰጠ ሆኖ ይታያል፡፡

### 4.1.5 የመ/ቁጥር 35913 እና የፍ/መ/ቁ 3/93

በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በቀረበ የፍቺ ጉዳይ አመልካች ባል፤ ተጠሪ ሚስት በሆኑበት አመልካች በ1971 ዓ.ም በሱዳን ሀገር በሃይማኖት ሥርዓት ጋብቻ መፈጸሙን ባል በሱዳን ሚስት በኩዌት አገሮች ኖረው በ1987 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው መኖራቸውን ገልጸው ፍቺና ውጤቱ እንዲወሰንላቸው አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ ግን ከጋብቻ ውጭ አንድ ልጅ በ1970 ዓ.ም መውለዳቸውን ጋብቻው የሐሰት መሆኑን ከ1987 ዓ.ም ወዲህ አብረው የኖሩት ከጋብቻ ወጭ እንደ ባልና ሚስት መሆኑን፣ አመልካቹ ሱዳን ሌላ ሚስት አግብቶ እንደኖረ እና ከ16 ዓመት በላይ መለያየታቸውንና ንብረቱን ያፈሩት በሰው አገር ብቻቸውን እየሰሩ መሆኑን ገልፀው የአመልካች አቤቱታ በሀሰት ንብረት ለመካፈል የቀረበ ነው በማለት ተሟግተዋል፡፡ የግራ ቀኙን ክርክር ያዩት የመጀመሪያ ደረጃና የከፍተኛ ፍ/ቤቶችም አመልካችና ተጠሪ ከ16 ዓመት በላይ ቢለያዩም ጋብቻው በፍ/ቤት ፍቺ ውሣኔ አልፈረሰም በማለት ወስነው በንብረት በኩል ተጠሪዋ በግሏ የገዛችውን ቤትና ሌሎችም ንብረቶች እንዲያካፍሉ ውሣኔ ሰጥተ ዋል፡፡[72]

በዚህ ጉዳይ በተሰጡት ውሣኔዎች በታዩት የሕግ አተረጓጎም ስልቶች ተጋቢዎቹ ለ16 ዓመታት ተለያይተው የጋብቻው ግላዊ ውጤት (ማለትም አብሮ መኖር፣ መረዳዳት፣

---

[71] አመልካቾች ዶ/ር አካለወልድ ገ/ሥላሴ፣ ተ ጠሪ ሲስተር ትርሲት ደስታ፣ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ የመ/ቁጥር 72399 /01/2/99/ /ያልታተመ/፡፡

[72] በዋና ይግባኝ ባይ ወ/ሮ አበዙ ገ/ያርያም፣ መልስ ሰጪ እና መስቀለኛ ይግባኝ ባይ አቶ ፈንታ መኳንንት፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፍ/ብሔር ይግባኝ ሰሚ፣ የመ.ቁ. 35913 / ሚያዝያ 17 ቀን 1999 ዓ.ም /ያልታተመ/፡፡

የግብረ ሥጋ ግንኙነት) ለረጅም ጊዜ በሌለበት ሁኔታ ጋብቻው በፍ/ቤት ባለመፍረሱ ሴቲቱ በሰው ሃገር ሠርታ ያፈራችውን ንብረት ወንድዬው ከሌላ ሚስት ጋር ዘመኑን ሲያሳልፍ ኖሮ ንብረት እንዲካፈል መወሰኑ የሴቲቱን መብት የጐዳውና በፍ/ቤቶች መድረክም እንባዋን ከማፍሰስ ያለፈ ውጤት አለማግኘቷን ያመለክታል፡፡ይህም የፍ/ቤቶቹ አቋም ሕጉን ንባቡን ተከትሎ በደረቁ መተርጐም በተከራካሪዎቹ ላይ ያለውን ውጤት የሚያመለክት ነው፡፡ ይህን መሰል አቋሞች በሀገር ቤት የአሜሪካን ዲቪ (Divesity Visa) ዕድል ለማግኘት ብለው የሃሰት ጋብቻ የሚመሠርቱትንና ጋብቻውን በፍ/ቤት ውሣኔ ሳያስፈርሱ አንደኛቸው መውጣት ሳይችሉ ቀርተው በተለያዩ አገሮች ለረጅም ዓመታት የሚኖሩትን በተመለከተ ምን ዓይነት ውጤት እነደሚኖረው መገመት ይቻላል፡፡

ከላይ ከተመለከተው ጉዳይ ጋር በይዘቱ ተመሣሣይ በሆነ በኦሮሚያ ክልል በአንድ ወረዳ ፍ/ቤት በታየ ጉዳይ፣ ባል የሰባት ልጆች እናት ሚስቱን ከድህነቷ ጋር ትቶ ለ15 ዓመታት ተለያይተው ሲኖሩ ከተለያዩ ሴቶች 8 ልጆች ከወለደ በኋላ ሚስት በግል ጥረቷ ሃብት ማፍራቷን አይቶ የፍቺ አቤቱታ ያቀረበበትና ቀለብም የተቆረጠለት አጋጣሚ እንደነበርም አቶ መለሰ ዳምጤ "ፍቺ በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት" በሚል ርዕስ በፃፉት ጽሑፋቸው የገለጹት ይታወሣል፡፡[73] ይህ ጉዳይ ባልና ሚስት ፍቺ ፈጽመናል በሚል ሃሣብ በፍ/ቤት ሣይፋቱ ለረጅም ጊዜ ከተለያዩ በኋላ አንደኛው ተጋቢ ሃብት ማፍራቱን ካረጋገጠ ጋብቻ አለኝ ብሎ መካፈል እንደሚችል ገምቶ ከቅን ልቦና ውጭ የክስ አቤቱታ በማቅረብ የሌላኛውን ወገን የንብረት መብቱን እንደሚጋፋውና በፍ/ቤት ድጋፍ ሊያገኝ እንደሚችል ያስረዳል፡፡

### 4.1.6 መ/ቁጥር 0127

በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 0127 ከተሰጠው ውሣኔ ለመረዳት እንደሚቻለው ደግሞ አመልካች ሚስት ወደ ትውልድ ሃገሯ ሄዳ እያለ ባል መሞቱን በመግለጽ በ1967 ዓ.ም በፈጸሙት ጋብቻ መሠረት በ1993 ዓ.ም የሞተው ባል ሚስትነቷ እንዲረጋገጥለት ትጠይቃለች፡፡[74] ሚች በሚሞትበት ጊዜ አብራው የነበረችው ሚስት ደግሞ በጉዳዩ በተቃዋሚነት በመግባት የአመልካቿን ሚስትነት ተቃውማ ተፋትተዋል ስትል ተከራክራለች፡፡ አመልካቿ በ1972 ዓ.ም የፍቺ ፋይል ከፍታ ጉዳዩ ለቤተዘመድ ጉባኤ ተመርቶ ለልጆቹ ቀለብ እየተከፈላቸው ጋብቻው በፍቺ ሣይፈርስ መኖሩን በመግለጽ ተሟግታለች፡፡ ፍ/ቤቱም የጣልቃ ገብን መቃወሚያ ባለመቀበል ጋብቻው አልፈረሰም በማለት የአመልካቿን ሚስትነት ከ22 ዓመት መለያየት በኋላ ወስኗል፡፡

አመልካቿ የተሰጣትን የሚስትነት ማረጋገጫ ማስረጃ በመያዝ የጡረታ መብት የጠየቀች ሲሆን በንብረት በኩል ጋብቻ በሚያስከትለው ውጤት ተጠቃሚ ለመሆንም ድጋሚ አቤቱታ አቅርባለች፡፡[75] በማመልከቻዋም የኋለኛዋን የሚችን ሚስት ተከሣሽ በማድረግ፣ "የእኔ ጋብቻ ሣይፈርስ ሚችና ተከሣሽ ከሠሩት ቤት ከሚች ድርሻ ግማሹን ታካፍለኝ" በማለት ጠይቃለች፡፡ ተከሣሿና በጉዳዩ ጣልቃ የገቡት ከተከሣሽ የተወለዱት የሚች ወራሾች ደግሞ ከሣሽ ከሚች ከተለያየች 25 ዓመታት ያለፈ መሆኑን በመጥቀስ ሚችና ተከሣሽ ያፈሩትን ንብረት ልትካፈል አይገባትምና ጥያቄው ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም "ከሣሽ ሚች ካላቸው ድርሻ ግማሹን ልትወስድ ይገባል? አይገባም?" የሚል ጭብጥ በመመሥረት አግባብ ካለው ሕግ ጋር መመርመሩን ገልጾ በውሣኔ ሃሣቡ

[73] አቶ መለሰ ዳምጤ ከላይ በቁጥር 68 በተመለከተው የተጻፈ፣ አመልካች አቶ አንበሴ ሙለታዩ ተጠሪ ወ/ሮ ዘውዲቱ ከበደ ቀርሳ ቆንዳሊቲ ወረዳ ፍ/ቤት፣ የፍ/መ/ቁ 3/93 /ያልታተመ/፡፡

[74] አመልካቶች እነ አዘነጋሽ ተክሉ /4 ሰዎች/፣ ጣልቃገብ ወ/ሮ እታየሁ አየለ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት፣ የመ/ቁ 0127 /4/2/96 /ያልታተመ/፡፡

[75] አመልካቶች እነ አዘነጋሽ ተክሉ /4 ሰዎች/ ተከሳሽ፤ ወ/ሮ እታየሁ አየለ የፌ.መ.ደ.ፍ.ቤት፣የመ.ቁ 03071 /22/9/99/ /ያልታተመ/፡፡

> "...የከሣሽ ክስ የባለቤቴ የሆነው ንብረት ከእኔ ጋር ያለው ጋብቻ ስላልፈረሰ የጋራ ንብረት ነው:: ባለቤቴ ካለው ድርሻ ግማሹን ተከሣሽ ታካፍለኝ የሚል ነው:: ተ ከሣሿም ሆነች ጣልቃ ገቦች በሰጡት መልስ ከሣሽ በቤቱ ላይ ምንም የገንዘብ አስተ ዋጽኦ አላደረገችም ምክንያቱም ከሟች ከተለያዩ ከ 25 ዓመት በላይ ሆኗቸዋል የሚል ነው:: ተለያይተው ለረጅም ጊዜ መቆየት ፍቺን አያስከትልም:: ጋብቻ በፍቺ ሊፈርስ የሚችለው በፍርድ ቤት ውሣኔ ብቻ እንደሆነ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 117 ይደነግጋል:: ስለዚህ የከሣሽና የሟች / በስም በመጥቀስ/ ጋብቻ በፍርድ ቤት ውሣኔ ፍቺ ስላልተደረገ ለረጅም ጊዜ ተለያይተው ቢኖሩም በሑ ሐከላቸው ያለው ጋብቻ እንደተጠበቀ ነው፤ ጋብቻ ካለ ደግሞ የጋብቻ ውጤቶች አብረው ይኖራሉ:: ከጋብቻ ውጤቶች አንዱ ደግሞ በጋብቻ ውስጥ የተፈራን ንብ ረት የጋራ ማድረግ እንደሆነ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 63/1/ ይደነግጋል:: ስለዚህ ከሣሽ ሟች ከተከሣሽ ጋር በትዳር አብሮ በመኖር ያፈሩት ቤት ግማሽ ባለቤ ት ናቸው:: የሟች ድርሻ ግማሹ የከሣሽ ነው ምክንያቱም በሟችና ከሣሽ መካከል ያለው ጋብቻ ሟች እስከ ሞት ድረስ አልፈረሰም"

በማለት ባልና ሚስቱ ቢለያዩም ጋብቻው አለመፍረሱንና ውጤት ያለው መሆኑን በተ ደጋጋመ ሁኔታ በመግለጽ በግንቦት 22 ቀን 1999 ዓ.ም ፍርዱን ሰጥቷል::

የሟች ወራሾችም ለከፍተኛው ፍ/ቤት ያቀረቡትን የይግባኝ ቅሬታ ለማጣራት ". . . ከሣሽና ሟች ለረጅም ጊዜ በተለያዩበት ዘመን ሟች ያፈሩትን ንብረት ጋብቻው በፍ/ቤት ባለመፍረሱ ብቻ ከሣሽ ሊካፈሉ ይገባልን?" የሚለው መከራከሪያ ጭብጥ ተይዞ እየተሟገቱበት እንደሚገኙ ከይግባኝ መዝገቡ ለመረዳት ተችሏል::[76]

ከላይ ከቀረበው የመጀመሪያ ደረጃው ፍ/ቤት የሚስትነትና የንብረት ክርክር ውሣኔ፣

ሀ. ባልና ሚስቱ አብሮ ለመኖር ባለመግባባታቸው በፍ/ቤት ክርክር ከፍተው ለልጆች ቀለብ ተቆርጦ የተለያዩ ሲሆን በፍ/ቤት ውሣኔ ተፋትተዋል ባለመባሉ ብቻ ባልዮው ሲሞት ከ22 ዓመት መለያየት በኋላ ሚስትነት መወሰኑን፣

ለ. ለረጅም ጊዜ መለያየት ቢኖርም ጋብቻው በፍ/ቤት እስካልፈረሰ ድረስ ጋብቻው በሕይወት እንዳለ እንደሚቆጠር አቋም መወሰዱንና የሕግ ትርጉም መስጠቱን፣

ሐ. ፍቺ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ መሠረት በፍ/ቤት ብቻ እንደሚወሰን በመደንገጉ ምክንያት የሕጉን ቀጥተኛ ንባብ ብቻ ተከትሎ መተርጐሙን፣ የባልና ሚስቱ ለ ረጅም ጊዜ መለያየትና ጋብቻ በግል ግንኙነት በኩል ያለው ውጤት መቋረጥ ጋብቻ በንብረት በኩል በሚኖረው ውጤት ላይ ለውጥ እንደማይኖረው ፍ/ቤቱ አቋም መውሰዱን ፣

መ. የሟች ወራሾች የውርስ ንብረት ከ 22 ዓመት በላይ ከአባታቸው ለተለየችው ሚስት በግማሽ በመሰጠቱ በውርስ የሚያገኙት የንብረት ሕገ መንግሥታዊ መብታቸው መጣበቡን፣ እንዲሁም ሌሎች አከራካሪ ነጥቦችን እንገነዘባለን::

#### 4.1.7 <u>የፌ/ከ/ፍ/ቤት መ/ቁ 29093</u>

አመልካች ለሁለት ዓመት በጋብቻ አብራው ከኖረችው ባለቤቷ ከ1961 ዓ.ም ጀምሮ ለ 34 ዓመት ያህል መለያየታቸውን ገልጻ በ1995 ዓ.ም ፍቺ እንዲወሰንላቸው ጠይቃ ካስወሰነች በኋላ የኋለኛዋ ሚስት ጣልቃ ገብታ ባልን ጨምሮ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተከራክረዋል። አመልካቿ ሌላ ባል አግብታ አምስት ልጆች መውለዷን፤ ባልዮው ከተ ቃዋሚዋ በፊት ሁለት ሚስቶችን አግብቶ በኋላም ተቃዋሚን አግብቶ እንደኖሩ በመግለጽ የአመልካችን የፍቺ ጥያቄ ተቃውማለች:: ፍ/ቤቱ የተቃዋሚን ክርክር ባለመቀበል የፍቺ ውሣኔውን ይሰጣል:: በመቀጠልም ፍ/ቤቱ በ34 ዓመታት ውስጥ

---

[76] ይግባኝ ባዮች እነ ወ/ሮ እታየሁ አየለ /3 ሰዎች/ መልስ ሰጪ ወ/ሮ አዘነጋሽ ተክሉ፣ የፌ/ከ/ፍ/ ቤት ይግባኝ ሰሚ፣ የመ/ቁ72399 /ያልተወሰነ/ በክርክር ላይ ያለ/::

ባልዮው ያፈራውን ንብረት ዝርዝር አመልካች እንድታቀርብ በመፍቀዱ ባል የፍቺውን ውጤት በተመለከተ እስከ ይግባኝ ድረስ ተከራክረው በፍቺ የንብረት ውጤቱ ላይ የተሰጠውን ብይን የፌ/ከ/ፍ/ቤት ሽሮታል፡፡[77]

#### 4.1.8 *የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መ/ቁ 04847 እና ሌሎች መዝገቦች*

የሟች ሚስቶች በነበሩ ሁለት ሴቶች መካከል በመጀመሪያ ደረጃው ፍ/ቤት በተካሄደ ክርክር አመልካች በ1972 ዓ.ም እማኞች ባሉበት በጋብቻ ውል ማፍረሻ ስምምነት ከሟች ጋር ተለያይተው ኖረው ሟች በ1987 ዓ.ም ሲሞቱ ሚስትነት አስወስነው የጡረታ መብት በመጠየቃቸው ተቃዋሚ ጋብቻው ፈርሷል በማለት ተሟግተዋል፡፡[78] ፍ/ቤቱ በባልና ሚስቱ መካከል የተደረገው የፍቺ ስምምነት ለሽምግልና ዳኞች ቀርቦ ፍቺ ባለመወሰኑ ፍቺ ተደርጓል ለማለት በቂ ማስረጃ አልቀረበም በማለት ከ15 ዓመት የባልና ሚስቱ በስምምነት መለያየት በኋላ ሚስትነት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ይግባኝ የቀረበለት የከፍተኛው ፍ/ቤት ጋብቻ ነበር ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት ይግባኙን ተቀብሎ ለማከራከር ቀጠሮ እንደሰጠ ባለጉዳዮች ባለመቅረባቸው መዝገቡ መዘጋቱን ለመረዳት ተችሏል፡፡[79] ይህ የመጀመሪያ ደረጃው ፍ/ቤት አቋም ባልና ሚስቱ በጽሑፍ ለመፋታታቸው ስምምነት ቢያደርጉም የሕጉን ፎርማሊቲ ስለማያሟላ ጋብቻው እንደፈረሰ አይቆጠርም የሚለውን አስተሳሰብ የሚጋራ ነው፡፡

በሌሎች መዝገቦችም በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 14871 ከ12 ዓመት መለያየት በኋላ ፍቺ የተወሰነበት፣[80] በመ/ቁ 26375 ከ23 ዓመት መለያየት በኋላ ባል ሲሞት ሚስትነት የተረጋገጠበት፣[81] በመ/ቁ 11799 ከ50 ዓመት በላይ መለያየት በኋላ ፍቺና የንብረት ክፍፍል የተወሰነበት፣[82] በመ/ቁ 36763 ጋብቻው በስምምነት ከተቋረጠ 12 ዓመት በኋላ የፍቺና ውጤቱ ውሣኔ የተሰጠበት[83] ወዘተ ፍቺ በፍ/ቤት እስካልተወሰነ ድረስ መለያየት እንደ ሕጋዊ ፍቺ አይቆጠርም ጋብቻውም አልፈረሰም የሚል አቋም የታየባቸው ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በእነዚህ ውሣኔዎች የታየው የዳኞች አስተሳሰብ ተጋቢዎች ለብዙ ዓመታት በእውነታው ቢለያዩም ጋብቻው በፍ/ቤት እስካልፈረሰ ድረስ ጋብቻው ከውጤቱ ጋር ይኖራል የሚል ነው፡፡ ይህንንም አቋም የሚደግፉ የሕግ ባለሙያዎች /ዳኞች/ ጋብቻ በፍ/ቤት ብቻ ይፈርሣል በማለት ሕጉ እስከደነገገ ድረስ እኛ ሕግ አውጭዎች ባለመሆናችን ውጤቱን ሣይሆን ሕጉ የሚለውን ብቻ ተከትለን መተግበር አለብን ይላሉ፡፡[84] የሌላኛውን አቅጣጫ የሚደግፉት ቁጥራቸው የሚያንሰው ባለሙያዎች /ዳኞች እንዲሁም የዩኒቨርስቲ የሕግ ምሁራን ደግሞ የጋብቻ ግላዊ ግንኙነት ውጤት ከተቋረጠና ጋብቻው በሕይወት ከሌለ

---

[77] ይግባኝ ባይ አቶ ቤተሥላሴ ገረሱ መልስ ሰጭ ወ/ሮ ደብረወርቅ ዘውዴ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የመ.ቁ. 29093 (9/3/98) (ያልታተመ)

[78] በመቃወም አመልካች ወ/ሮ ፀሐይ ዓለሙ፣ በመቃወም ተጠሪ ወ/ሮ ጽጌ ተክለወልድ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የመ.ቁ 04847 (19/4/98) /ያልታተመ/፡፡

[79] ይ/ባይ ወ/ሮ ጽጌ ተክለወልድ መልስ ሰጭ ወ/ሮ ፀሐይ ዓለሙ የፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ሁለተኛ ችሎት የመ.ቁ. 43868 /ያስቀርባል ከተባለ በኃላ ባለጉዳዮች መጥሪያ ባለማድረሳቸው የተዘጋ/፡፡

[80] አመልካች አቶ ኃይሉ ገ/መድህን /ተተኪ ወራሾች/፤ ተጠሪ ወ/ሮ ለተንሳይ በርሄ፤ ጣልቃገብ ወ/ሮ ፅጌወይኒ አብርሃ፣ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ የመ/ቁ 14871/3-4-99/ /ያልታተመ/፡፡

[81] አመልካች ወ/ሮ ክበበ ፋንታ፤ ተጠሪ ወ/ር አየለ ገ/ህይወት፤ ጣልቃ ገብ ወ/ሮ አለምነሽ አብዶ፣ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት፣ የመ/ቁ 26375 / 03/09/98/ /ያልታተመ/፡፡

[82] አመልካች ወ/ሮ ሙላቷ መንገሻ፣ ተጠሪ አቶ ተኮላ ፈጠነ፣ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የመ/ቁ 11769፣ /24/8/99 / /ያልታተመ/፡፡

[83] አመልካች ወ/ሮ አልማዝ ተስፋዬ፤ ተጠሪ አቶ ብርሃኔ ጉልላት፣ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የመ/ቁ36763 /11/4/99 ዓ.ም. /የፍቺ ውሣኔ እና 11/11/99 ዓ.ም. የንብረት ክፍፍል ውሣኔ/ /ያልታተመ/፡፡

[84] ከላይ በቁጥር 25 ከተመለከተው የተወሰደ

ወይም በእውነታው ከፈረሰ በኋላ ጋብቻውና የንብረት ውጤቱ አለ ማለት ተቀባይነት ያለው ትርጉም አይደለም በማለት ይከራከራሉ::[85]

#### 4.1.9 የትግራይ ክልል ፍ/ቤት ውሳኔዎች

"ሳይፋቱ" (ዲ ፋክቶ) ፍቺን የሚመለከቱ ውሣኔዎች ልዩነትና አከራካሪነት በትግራይ ክልል ፍ/ቤቶች በተሰጡ ውሣኔዎችም ተንፀባርቋል::[86] በዚህ ጉዳይ አመልካች (ሚስት) ለማህበራዊ ፍ/ቤት ባቀረበችው አቤቱታ ከተጠሪ ባለቤቷ ጋር የፍቺና ውጤቱ ውሣኔ እንዲሰጥላት በ1998 ዓ.ም አመለከተች። ተከሣሽ ባል ደግሞ በ1989 ዓ.ም በሽምግልና ጉባኤ የፍቺና ውጤቱ ውሣኔ ተለያይተው የየግል ኑሯቸውን እንደሚኖሩና ሌላ ሚስት አግብቶ ልጆች ወልዶ መኖር ከጀመረ 10 ዓመት በኋላ የቀረበው የፍቺ ጥያቄ ውድቅ ይሁን ሲል ይከራከራል:: ማህበራዊ ፍ/ቤቱ ቀድሞ ፍቺ መደረጉን በመቀበል ከሣሽን ተረቺ፤ ተከሣሽን ረቺ በማድረግ ይወስናል:: ይግባኝም ለወረዳ ፍ/ቤት ቀርቦ ተቀባይነትን ያጣል። በክልሉ የመጨረሻ ደረጃ የሆነው 5 ዳኞች የተሰየሙበት የክልሉ የሰበር ችሎት ደግሞ የከሣሽን የሰበር አቤቱታ መርምሮ "የፍቺ ውሣኔ ሊሰጥ የሚቻለው ፍርድ ቤት ብቻ በመሆኑ ከዚህ ውጭ በሕግ ተቀባይነት ስለሌው በሽምግልና ተፋተናል የሚለው ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 729 ሲገናዘብ ተቀባይነት የለውም" በማለት በሁለቱ ወገኖች መካከል ያለው ጋብቻ ከ11/07/99 ጀምሮ እንዲፈርስ ወስኗል። በፍቺ ውጤቱም ውሣኔ አመልካቿ ተከሣሽ ከሌላ ሚስት ጋር በ10 ዓመት ውስጥ ያፈሩትን ሃብት ለመካፈል እድል አግኝተዋል:: በዚህ የክልሉ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም አቤቱታውን ባለመቀበል ቅሬታ አቅራቢውን ማሰናበቱን ለመረዳት ተችሏል::[87]

### 4.2 የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ

እስከ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የደረሰና "ሳይፋቱ" ፍቺን የሚመለከት ከ10 ዓመት በላይ ክርክር የወሰደ ጉዳይ ቀጥለን እንመለከታለን። አቶ በየነ መራጭ ጳጉሜ 3 ቀን 1987 ዓ.ም መሞታቸውን የሥር አመልካች ወ/ሮ እታገኘሁ አድማሱ ገልጸው ሚስትነታቸው እንዲረጋገጥ ባመለከቱበት መዝገብ ተቃዋሚ ወ/ሮ አበበች የሽዋሉል አመልካችና ሟች ከተለያዩ 13 ዓመት ማለፉንና አመልካች ሌላ ባል አግብተው የ11 ዓመት ልጅ ያላቸው መሆኑንና ጋብቻቸው መፍረሱን በመግለጽ ይከራከራሉ:: የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ጋብቻ ነበር መፍረሱ አልተ ረጋገጠም በማለት ሚስትነትን በታህሣስ 22 ቀን 1995 ዓ.ም ውሣኔው አረጋግጧል:: የዚህ ውሣኔ ተቃዋሚ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ ብታቀርብም በመ/ቁ 16731 በ25/2/96 በተ ሰጠ ዳኝነት ይግባኙ ተቀባይነት አላገኘም።

የሥር ተቃዋሚ በሁለቱ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔዎች ተስፋ ሳትቆርጥ አቤቱታዋን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርባ መልስ ሰጭ ተጠርተው ችሎቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ በሰ/መ/ቁ 14290 መጋቢት 25 ቀን 1999 ዓ.ም ፍርድ ሰጥቶበታል::[88] ችሎቱ

---

[85] ከላይ በቁ-23 እና 24 ከተጠቀሱት የተወሰደ::

[86] አመልካች ወ/ሮ አባዲት ገ/የሱስ፣ ተጠሪ አቶ ግደይ በላይ፣ የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣ የጠቅላይ ፍ/ቤት የመ.ቁጥር 16999 17/9/99/ የእንደማርያም ወረዳ ፍ/ቤት የመ.ቁ 1/98/5/11/98/ ከዋኒት ቀበሌ ገበሬ ማህበር ማህበራዊ ፍ/ቤት 19/10/98/ /ያልታተመ/::

[87] ከአቶ ስሜነህ ተክሉ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ጠበቃ ጉዳዩን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ካቀረቡት የተወሰደ መረጃ::

[88] የሰበር አመልካች ወ/ሮ አበበች የሽዋሉል፣ መልስ ሰጪዎች እነ ወ/ሮ እታገኘሁ አድማሱ /ጉዳዩ የሚመለከተው 1ኛ መልስ ሰጭን ብቻ ነው/፣ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር መ.ቀ 14290 /መጋቢት 25 ቀን 1999 ዓ.ም/ /ያልታተመ/ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት፣ መ.ቁ. 01579 /126/88 በ 22/04/95 የተወሰነ/:: (በሚቀጥለዉ ገጽ ይመልከቱ)

ከመልስ ሰጭ ምስክሮች መልስ ሰጭ ከሟች ጋር ጋብቻ እንደነበራት ይሁንና ከ13 ዓመት በፊት መለያየታቸውን፣ ሌላ ግለሰብ አግብታ ትኖር እንደነበር፣ በዚህም ግንኘ-ነት የ11 ዓመት ልጅ እንደወለዱና ባለቤታቸውም በ1984 መሞታቸውን ማረጋገጡን በመመዝገብ የሚከተለውን ወስኗል፡፡

"ግንኙነቱ በሕጋዊ መንገድ መቋረጡ እስካልተረጋገጠ ድረስ ግንኙነት ተቋርጧል ማለት አይቻልም የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም፡፡ ከመዝገቡ ግልባጭ ለመረዳት እንደሚቻለው የሁለቱ ግንኙነት ሟች ከሞመታቸው በፊት ለአሥር ዓመታት ያህል ግንኘ-ነታቸው ተቋርጦ እንደነበር ከላይ ከተቀመጡት ፍሬ ነገሮች ለመረዳት ስለሚቻል ተ ጋቢ ነበሩ የተባሉ ሁለት ሰዎች ከአቅም በላይ ባልሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ለዚህን ያህል ጊዜ ተለያይተው ቆይተዋል ከተባለ ግንኙነታቸው እንደቀጠለ ነበር ለማለት አያስደፍርም ፡፡ በእውነታ ደረጃ ተለያዩ እንጂ በሕጋዊ መንገድ ስላልተለያዩ ግንኙነቱ ሕጋዊ ውጤት ሊያስከትል ይችላል ለማለትም አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ መልስ ሰጭ ከሟች አቶ በየነ መራጭ ጋር ተለያይተው በነበረበት ጊዜ ሌላ ትዳር መስርተው የመኖራቸው እውነታ ከአቶ በየነ መራጭ ጋር የነበራቸው ግንኙነት በሕጋዊ መንገድ ተቋርጦ ነበር ለሚለው የጎላ ግምት በቂ መነሻ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡. . . የመልስ ሰጭ የሰው ማስረጃዎች መልስ ሰጭ እና ሟች አቶ በየነ መራጭ ከዛሬ 13 ዓመት በፊት አብረው መኖር አቁመዋል ተለያይተዋል ሲሉ የሰጡትን ቃል ከላይ ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ፍሬ ነገሮች ጋር አዛምደን እንደተመለከትነው በመልስ ሰጭ እና በሟች አቶ በየነ መራጭ መካከል ተፈጥሮ የነበረው ግንኙነት በሕጋዊ መንገድ ተቋርጦ የነበረ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም መልስ ስጭ የሟች አቶ በየነ መራጭ ሚስት ናቸው በሚል የተሰጠውን ዳኝነት አልተቀበልነውም»

በማለት የመጀመሪያ ደረጃውንና የከፍተኛውን ፍ/ቤቶች ውሣኔና ትዕዛዝ (በቅደም ተከተ ላቸው) በመሻር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

በተመሣሣይ መልኩ ሰበር ሰሚ ችሎቱ በመ/ቁ 20938 ሚያዝያ 11 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የጋብቻ መፍረስን የማስረዳት ጭብጥ በመያዝ ወጥነት ያለው ተመሳሳይ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በዚህ ጉዳይ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች በሞት የተለዩት ባለቤታቸው  ሚስትነት እንዲወሰንላቸው አመልክተው የሟች ሁለተኛ ሌላ ሚስት ደግሞ እኔ ነኝ የሟች ሚስት የሚል ተቃውሞ አቅርበው ተከራክረዋል፡፡ ሚስትነት እንዲረጋገጥ ያመለከተችው ሴት ከሟች ጋር በ1966 መጋባታቸውን፣ የጋብቻ ግንኙታቸውን ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ ያቋረጡ መሆኑን፣ ሟች አመልካችን አግብቶ አካባቢ መቀየሩን እንደ ሰማች፣ ጋብቻው ግን  በፍቺ አለመፍረሱንና ሟችም በ1989 ዓ.ም መሞቱን አስረድታ ጋብቻው ባለመፍረሱ ሚስተነቷ እንዲወሰንላት ተሟግታለች፡፡ የመጀመሪያ ደረጃው ፍ/ቤትም ተጠሪና ሟች ቢለያዩም ጋብቻው አልፈረሰም በማለት ሚስትነትን አረጋግጦ የወሰነ ሲሆን ከፍተኛው ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ በመሠረዝ የሚስትነቱን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡[89]

የተጠሪን የሚስትነት ጥያቄ  የተቃወመች ሁለተኛ ሚስት ለሰበር አቤቱታዋን አቅርባ ተጠሪ ተጠርታ ከተከራከሩ በኋላ የሰበር ሰሚ ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ ሲወስን፣

> ". . . ከዚህ መገንዘብ የቻልነው የአሁንዋ መልስ ሰጭ ምንም እንኳ ከሟች ጋር ቀደም ብሎ የተፈፀመ ጋብቻ የነበራቸው ቢሆንም በመካከላቸው በተፈጠ ረ አለመግባባት ምክንያት በነበረው ጋብቻ መቀጠል አለመቻላቸውንና ሁለቱ በየፊናቸው የየራሣቸውን ሕይወት መጀመራቸውን ነው፡፡  የአሁን መልስ ሰጭ

[88] (የተቀጠለ) የፌ/ከ/ፍ/ቤት፣ መ.ቁ. 16731 / በ25/2/96 ትዕዛዝ የተሰጠበት/

[89] የሰበር አመልካች ወ/ሮ ሸዋዬ ተሰማ፤ መልስ ሰጭ ወ/ሮ ሣራ ልንጋን፣ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የመ/ቁ. 20938 /ሚያዝያ 11 ቀን 1999 ዓ.ም /በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤ ት ሰበር ሰሚ ችሎት ፍርዶች በቅጽ 4 የታተ መ/ ገጽ 85-87፡፡

*ጋብቻው በፍቺ ምክንያት አልፈረሰም የሚል እንጂ ለፍ/ቤቱ የሰጡት ማረጋገጫ ጋብቻው መፍረሱን የሚያረጋግጥ ነው፡፡"*

በማለት ተጠሪ ከ1985 ጀምሮ ከሟች ጋር የተለያዩ መሆኑን ትኩረት ሰጥቶታል በመቀጠልም

> *"ጋብቻ የሚፈርሰው ሕጉ ባስቀመጣቸው ውሱን ምክንያት መሆኑን ይህም ፍ/ቤት ይቀበለዋል፤ በሌላ በኩል ለጋብቻ መፍረስ ምክንያት የሆኑ ነገሮች መኖር አለመኖራቸውን የሚረጋገጠው እንዴት ነው? የሚለው ጥያቄና ነጥብ በሁለቱም ተ ጋቢዎች ከነበረው ሁኔታ ጭምር መረዳት የሚቻል ነው፡፡ ጋብቻ የሚፈርስበትን ምክንያት መፍረሱን ከማስረዳት መለየትም ያስፈልጋል፡፡ አሁን በቀረበልን ጉዳይ የመልስ ሰጭ መከራከሪያ ፍቺ መፈጸሙን አመልካች አላስረዳችም የሚል ነው፡፡ ነገር ግን የመልስ ሰጭና የሟች ግንኙነት ማንም ሌላ ማስረጃ ሊያስረዳ ከሚችለው ከሚገልጸው በላይ በመካከላቸው የነበረው የጋብቻ ግንኙነት መፍረሱ ሁለቱም ሌላ ሕይወት ጀምረው ሟች የአሁንዋን አመልካች ማግባታቸውን ይህንንም ጋብቻ የአሁኗ መልስ ሰጭ ያውቁ እንደነበር ያስረዳል፡፡ ይህ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ የአሁንዋን መልስ ሰጭ ቀደም ሲል የፈጸመችውን ጋብቻ መሠረት በማድረግ ብቻ ሚስት ናት ብሎ መወሰኑ ትክክለኛ የሕግ አተረጓጐም አይደለም"*

በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሮ መልስ ሰጭ የሟች ሚስት አይደለችም በማለት ወስኗል፡፡

ይህ በሰበር ችሎት ፍርድ የተሰጠው የሕግ ትርጉም ፍርዱ ለተሰጠበት ጉዳይ ዕልባት ከመስጠት ባሻገር፣ በአዋጅ ቁጥር 454/97 መሠረት በበታች ፍ/ቤቶች ላይ በተመሳሳይ የሕግ ጭብጥ አተረጓጐም ረገድ አስገዳጅነት አለው፡፡ የሕግ ትርጉሙ በጽሑፉ ምልከታ በተደረገባቸው ፍርዶች የታዩትን የሕግ አተረጓጐምና የውሣኔ አሰጣጥ ልዩነቶችን የሚያስታርቅና የሕጉን ዓላማ፣ የሕጉን መንፈስና ውጤትን መሠረት አድርጐ መወሰን እንዳለበት የሚያሳይ ነው፡፡

የሰበር ችሎቱ ውሣኔ የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች ያካተተ መሆኑን መመልከት ይቻ ላል፡፡

ሀ. የባልና ሚስት መለያየት ብቻውን በቤተሰብ ሕጉ አንቀፅ 117 መሠረት በፍ/ቤት ፍቺ እስካልወሰነ ድረስ የጋብቻ ግንኙነት እንደተቋረጠ አይቆጠርም የሚል አስተ ሳሰብ /አቋም መኖሩን ከወዲሁ ከግምት አስገብቷል። ያለ ፍ/ቤት የፍቺ ውሳኔ መለያየትን እንደ ፍቺ በመቁጠር ከመደምደሚያ የደረሰውም ተቃራኒ አቋሙን ከጅምሩ በማመልከት ነው፡፡

ለ. የባልና ሚስቱ ግንኙነት ከባል መሞት በፊት ለረጅም ጊዜ ተቋርጦ የነበረ መሆኑን ከክርክሩ ፍሬ ነገር የተረዳውን ሁኔታ በፍርዱ እንደ ፍቺ የግምት ማስረጃ ተ ጠቅሞበታል፡፡

ሐ. የተጋቢዎቹ መለያየት ከአቅም በላይ በተከሰተ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ለረጅም ጊዜ ተለያይተው ከቆዩ የጋብቻ ግንኙነታቸው እንደቀጠለ ነው (ነበር) ማለት እንደማይችል ፍርድ ቤቱ ገልጿል፡፡

መ. በእውነታ ደረጃ የተለያዩ ባልና ሚስት በሕጋዊ መንገድ ማለትም በፍ/ቤት ውሣኔ ስላልተለያዩ ግንኙነቱ ሕጋዊ የጋብቻ ውጤት ሊያስከትል ይችላል ለማለት እንደሚያስቸግር አስምሮበታል፡፡ ይህም ጋብቻው በፍ/ቤት በሕግ እስካልፈረሰ ድ ረስ ተጋቢዎቹ ቢለያዩም የጋብቻ ውጤቱ ይኖራል የሚለው አቋም (የአተረጓጐም ሥልት) ችግር የሚያስከትል መሆኑን መረዳቱን ያመለክታል፡፡

ሠ. የሚስትነት ይረጋገጥልኝ አቤቱታ አቅራቢ ከሌላ ሰው ጋር ጋብቻ መሥርተው ልጅ የመውለዳቸውንም ፍሬ ነገር /እውነታ/ አስቀድሞ የነበራቸው ጋብቻ በሕጋዊ መንገድ ተቋርጦ ነበር ለሚለው የጉላ ግምት መነሻ ሆኖ ማግኘቱን መግለጹ ተጋቢ

ዎች ከቀድሞ ጋብቻቸው ተጋቢ ተለያይተው ሌላ ጋብቻ ከመሠረቱ የቀደመው ጋብቻ በሕጋዊ መንገድ እንደተቋረጠ የሕግ ግምት ሊወሰድበት እንደሚገባ ፍ/ቤቱ የሕግ ትርጉም መስጠቱን ያስረዳል፡፡

ረ. የሰበር ችሎቱ ከላይ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች /ፍሬ ነገሮች መሠረት በማድረግ በመልስ ሰጭና በሚች መካከል ተፈጥሮ የነበረው ግንኙነት በሕጋዊ መንገድ ተ ቋርጦ የነበረ መሆኑን ግንዛቤ መውሰዱና መልስ ሰጭ ሚስት አይደሉም ሲል ዳኝነት መስጠቱ፣ ፍቺ የግድ በቤተሰብ ሕጉ መሠረት በፍ/ቤት ውሣኔ ብቻ ሳይሆን በእውነታው በተለይም በረጅም ጊዜ መለያየት ፍቺ እንደተፈፀመ ግምት ሊወስድበት እንደሚገባ የሕግ ትርጉም መስጠቱን ያስረዳል፡፡ ይህም የሕግ ትርጉም ጋብቻ ሕጋዊ ውጤት እንዲኖረው በሕጉ በአስገዳጅነት የተደነገገውን የአብሮ መኖር ውጤት መከወን አስፈላጊ መሆኑንና በተቃራኒው በብዙ ዓመታት መለያየት ካለ ግን የግንኙነቱ ሕጋዊ ውጤት እንደሚቋረጥ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ሰ. በተጨማሪነት ከሁለተኛው ጉዳይ ውሣኔ የተጋቢዎቹ መለያየት በተከራካሪዎች እምነትም ሆነ በሌላ መንገድ ከተረጋገጠ ፍቺ በፍ/ቤት መፈጸሙን ማስረዳት ሳያስፈልግ ፍቺ ለመፈፀሙ የሕግ ግምት ሊወሰድበት እንደሚችል፣ ሁለቱ ተጋቢ ዎች በየፊናቸው የራሣቸውን ሕይወት መጀመራቸው ማለትም ከሌላ ጋብቻ መፈፀማቸው መፋታታቸውን እንደሚያስረዳ ፣ እንዲሁም ጋብቻ መኖር አለመኖሩን ከተጋቢዎቹ የኑሮ ሁኔታም መረዳት እንደሚገባ፣ ጋብቻ የሚፈርስበትን ምክንያት ማስረዳት መፍረሱን ከማስረዳት የተለየ መሆኑን፣ ይኸውም በፍ/ቤት ፍቺ ተፈጽሟል/ አልተፈጸመም የሚለውን የፎርም ጥያቄ ብቻ ሣይሆን ተጋቢዎቹ የጋብቻን ግላዊ ውጤት በእውን ተግባራዊ ማድረግ አለማድረጋቸው መታየት እንዳለበት ፍ/ቤቱ መወሰኑን ያስረዳል፡፡ በዚሁ መሠረት ለትክክለኛ የሕግ አተ ረጓጐም ጋብቻ በፍ/ቤት ፈርሷል /አልፈረሰም/ የሚለውን ነጥብ ብቻ ሳይሆን ማናቸውም ማስረጃ ከሚያስረዳው በላይ በተጋቢዎቹ መካከል ያለው ግንኙት ማስ ረጃ ሊሆን የሚችል መሆኑን ከግምት ማስገባት እንደሚያስፈልግ ያስረዳል፡፡

ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ነጥቦች መረዳት የሚቻለው ሕጉ በጠባብ ንባቡ ብቻ መተ ርጐም እንደሌለበትና የሕጉን ዓላማና መንፈስ እንዲሁም ማህበራዊ እውነታን ከግምት ማስገባት እንደሚያስፈልግ ነው፡፡ በሀገራችን በፌዴራሉም ሆነ በክልሎች ግዛት በተ ለይም በክልሎች ወደ ፍ/ቤት ሳይመጡ ወይም በሽምግልና ወይም በራሣቸው በተጋቢዎ ቹ ስምምነት ወይም ሰማንያ በመቅደድ የሚለያዩና በእውነታው ፍቺ የሚፈጽሙ በርካታ ተጋቢዎች ስለመኖራቸው በግልጽ የሚታወቅ ነው፡፡ እውነታው ከተግባሩ አንፃር ሲታይም ለብዙ ጥንዶች ሕጉ ለጋብቻ መግቢያ አፈፃፀም ሥርዓት ሦስት መንገዶችን ሠርቶ /ፈቅዶ/ ከጋብቻ በፍቺ ሲወጣ ለፍቺ አፈፃፀም ሥርዓት አንድ መንገድ ብቻ በሕጉ የተደነገገ መሆኑ በባህል ሕግ ለመፋታት የተሰጠውን መብትም ሆነ እውነታውን ያገናዘበ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሰበር ሰሚ ችሎቱ ረጅም ጊዜ መለያየትን እንደ ፍቺ ማስረጃ ሲመለከተው፣ በየትኛው ሕግ እንደተፋቱ ሊቆጠር ነው? የሚለው ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም፡፡ ስለሆነም ይህን ክፍተት በተመለከተ ሰፊ ጥናት ማድረግና መፍትሔ መስጠት ተገቢ ነው፡፡

## ማጠቃለያና የመፍትሔ ሃሣቦች

ቤተሰብ የኅብረተሰብ የተፈጥሮ መነሻ መሆኑንና በኅብረተሰቡና በመንግሥት ጥበቃ ሊደ ረግለት የሚገባ መሆኑ በሕገ መንግሥቱና የቤተሰብ ሕጉ ተመልክቷል፡፡ በክልሎች ሕግጋትም ተመሣሣይ ጥበቃ ተደርጐለታል፡፡ የቤተሰብ ተቋም የሚቋቋምበት አንደኛው ሥርዓት ጋብቻ ሲሆን ሕጉ በጋብቻ አፈፃፀም፣ በጋብቻ ዘመንና በፍቺ ጊዜ የተቋሙንና የተጋቢዎችን ጨምሮ የቤተሰብ አባላትን መብት ያስከብራል፡፡ ይህንን ዓላማና ግብ መሠ ረት አድርጐ በጋብቻ ሥርዓት የቤተሰብ ተቋም መሥራች በሆኑት ተጋቢዎች መካከል አለመግባባቶች ሲፈጠሩ ሕጉ የሚዳኝበትን የመፍትሔ መንገዶችን ሠርቷል፡፡ በሕገ መንግሥቱ የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሃይማኖት ወይም በባሕሎች ሕጎች መሠረት መዳኘትን ያልከለከለ ሲሆን ሕገ መንግሥቱን ተከትሎ

የወጣው የቤተሰብ ሕግ ግን መሠረታዊ የባልና ሚስት አለመግባባት ውጤት የሆነው የፍቺና ውጤቱን ክርክር በፍ/ቤት ብቻ እንዲወሰን የሚያደርግ ነው፡፡

የተለያዩ የብሔር፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦች የባህልና የሃይማኖት እሴቶች ከሕጉ እስካልተጋጩ ድረስ በሕገ መንግሥቱ እንደ ዲሞክራሲያዊ መብት የሚቆጠሩ ናቸው ዳሩ ግን የቤተሰብ ሕጉ ትልቁ የባሕል እሴታችን የሆነውን ባህላዊ ሽምግልና ዳኝነትን ከፍቺ በመለስ ከሚነሱ አለመግባባቶች በስተቀር እንደ አማራጭ ሙግት መፍቻ ዘዴ እውቅና ያልሰጠ በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ የተጠበቀውን መብት አጥብቦታል ለማለት ይቻላል፡፡

በሕጉ ጋብቻ የሚፈጸምበት ሥርዓት ሦስት ዓይነት አማራጭ እድሎች ያሉት ሲሆን ሕጉ ለፍቺ ሥርዓት አንድ ዓይነት መንገድ ብቻ ሠርቷል፡፡ ይኸውም ፍቺ በፍ/ቤት ብቻ እንዲፈፀም የሚያስገድድ በመሆኑ በሀገራችን በተግባር በተለይም ከ80% በላይ በሚኖርበት በገጠሩ ማኅበረሰብ በልዩ ልዩ ባህላዊ መንገድና በስምምነት ከመፋታቱ እውነታ ጋር የማይታረቅ ግጭት ያለው መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡ የቤተሰብ ሕጉ የጋብቻ ምዝገባ ሥርዓት ሠርቶ ተቋሙ ባለመቋቋሙና የምዝገባ ሥርዓትም በመደበኛ መልኩ በማይከናወንበት ሁኔታ ያልተመዘገበ ጋብቻን በፍ/ቤት ብቻ ይፍረስ ብሎ ማስገደዱ ከተደራሽነቱም ሆነ ከአፈፃፀሙ ተግባራዊነት አንፃር አከራካሪ ጉዳይ ነው፡፡

የቤተሰብ ሕጉ ከ50 ዓመት በፊት የነበረውን በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ በሽምግልና የፍቺን ውሣኔም ያስቀረ፣ በዘመናችን እያደገ ያለውን አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገድንና የሕግ ዘርፈ ብዙነት ጽንስ ሃሣብ ያላገናዘበ ነው፡፡

የሕጉ አንቀጽ ንባባዊ ትርጉም (literal reading) ከሕጉ ዓላማና ምክንያታዊነት የሚፃረር ትርጉም በሚሰጥበት ጊዜ ለሕጉ ተስማሚ ትርጉም መስጠት ከፍርድ ቤቶች ይጠበቃል፡፡ ይሁን እንጂ ለዓመታት በእውነታው የተለያዩትንና ሌላ ጋብቻ የመሠ ረቱትን ጭምር ፍርድ ቤቶች ሲያፋቱና የፍቺ ውጤቱን ሲወስኑ ይስተዋላል፡፡

ስለሆነም በፍርድ ቤት ፍቺ ሳይፈጽሙ በተግባር (ዲፋክቶ) ለብዙ ዓመታት ተለያይተው የቆዩ #ባልና ሚሰት; በሚመለከት ፀሐፊው የሚከተሉትን የመፍትሔ ሃሣቦች ይሰነዝራል፡፡

ሀ. ሕጉ በሥራ ላይ እስካለ ድረስ ተጋቢዎች ጋብቻቸውን እንዲያስመዘግቡና በፍቺም ሲለያዩ በፍ/ቤት መፋታት ግዴታ እንዳለባቸው እና አጠቃላይ ስለቤተሰብ ሕጉ ለኅብረተሰቡ በመገናኛ ብዙሃንም ሆነ በሌሎች መንገዶች ማስተማርና ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

ለ. ፍ/ቤቶች የቤተሰብ ሕጉን በተለይ ፍቺንና ውጤቱን የሚመለከቱትን ድንጋጌዎች ሲተረጉሙ በደረቁ የመከነ ትርጉም በመስጠት ሳይሆን ሕይወት ያለውና ከነባራዊ እውነታው ጋር በሚስማማ መልኩ ተግባራዊ ሊያደርጉት ይገባል፡፡

ሐ. የቤተሰብ ሕጉ የቤተሰብ ነክ አለመግባባትን በሕገ መንግሥቱ የተፈቀደውን በሃይማኖትና በባሕል ሕጎች የመዳኘትን መብት ያጣበበ በመሆኑ በተለይም በአንቀጽ 117 ፍቺና ውጤቱ በፍ/ቤት ብቻ እንዲወሰን የተደነገገው በሕግ አውጭው ሊሻሻልና የባህልና የሃይማኖት ዳኝነትን በተጋቢዎች ፈቃድ እንደ አማራጭ ዕውቅና ሊሰጠው ይገባል፡፡ በተለይም የፌዴራሉን ሕግ ተከትለው ፍቺን በፍ/ቤት ብቻ እንዲከናወን በመደንገግ የቤተሰብ ሕግ ያወጡ ክልሎችም አንቀጹን ቢያሻሽሉ ይመረጣል፡፡ የቤተሰብን ሕግ ለክልሎች የማውጣት ሥልጣኑ መሰጠቱም ይህንኑ መሰል ልዩነቶችን ለማስተናገድ እንዲቻል መሆኑ ይታመናል፡፡

መ. ባልና ሚስት ለረጅም ጊዜና በዘለቄታነት በሽማግሌም ሆነ በራሳቸው ፈቃድና ስምምነት ተለያይተው የሚኖሩ ከሆኑ ፍቺ እንደፈጸሙ ግምት

የሚወሰድበትን (Legal Presumption) የሚፈቅድ በሕግ ማሻሻያ ሊኖር ይገባል በአማራጩ ፍቺ በፍ/ቤት ብቻ ይወሰን የሚባል ቢሆን ደግሞ ለረጅም ጊዜ በእውነታ የተለያዩ ባልና ሚስት የፍቺ ውሳኔ ሲጠይቁ ፍቺው በንብረት በኩል ስለሚኖረው ውጤት በተለያዩበት ዘመን በየግላቸው ያፈሩት የግላቸው እንዲሆን የሕግ ማዕቀፍ ሊሰራ ይገባዋል፡፡ እንዲሁም እጅግ ለተራዘመ ጊዜ ከተለያዩ በኋላ የፍቺና ውጤቱን ክስ ማቅረብ በሕጋችን ውስጥ ከተካተተው የይርጋ መርህ ጋር ስለሚቃረን የይርጋ ደንብ ሊደነገግ ይገባዋል፡፡

ሠ. የፍቺና ውጤቱ ክርክር በማናቸውም ወቅት ከጋብቻና ውጤቱ ጋር ተገናዝቦ የሕግ ትርጉም ሊሰጥበት ይገባል፡፡

ከላይ የቀረቡት ሃሳቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የቤተሰብ ሕጉ እስከሚሻሻል ጊዜ ድረስ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ. 14290 መጋቢት 25 ቀን 1999 ዓ.ም. እና በሰበር መ/ቁ 20938 ሚያዝያ 11 ቀን 1999 ዓ.ም. «ሳይፋቱ» (ዲ ፋክቶ) ፍቺን በተ መለከተ የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 454/97 መሠረት በሁሉም ፍ/ ቤቶች ተመሳሳይ ጭብጦችን በመተርጐም ረገድ ተፈፃሚነት ሊኖረው ይገባል፡፡ ማለትም፣ ለረጅም ጊዜ መለያየተና ለምሳሌም ከተለያዩ በኋላ ሌላ ትዳር መመሥረት በሰበር ችሎቱ አገላለጽ ማንም ሌላማስረጃ ሊያስረዳ ከሚችለው ከሚገለፀው በላይ» (a fortiori) ጋብቻ መፍረሱን ያረጋግጣል፡፡

ከዚህም በተጓዳኝ በአገር አቀፍ ፍ/ቤቶች ማሻሻያ የ2000 ዓ.ም በጀት ዓመት እቅድ ላይ የአማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓትን (ADR) በፌዴራል፣ በክልሎችና በአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ከማቋቋም ባሻገር ይህንኑ በሥራ ላይ ማዋል ያሻል፡፡ በዚህ ረገድ ከፍ/ ቤቶች እና ከሌሎች ባለድርሻዎች ጋር ለመወያየት እና በሌሎችም ጉዳዮች በተያዘው እቅድ መሠረት እንዲሁም ወደፊት በሚያዙት እቅዶች በጽሑፉ የቀረበው ችግር በሕግ መሻሻልም ሆነ በሌላ መንገድ በሚመለከታቸው አካላት መፍትሔ ሊሰጠው ይገባል፡፡ በመጨረሻም በዚህ ጽሁፍ ለተመለከትነው የሕግ ክፍተትና የሕግ አተረጓጐም ጽንፋዊ ልዩነት መፍትሔ ማግኘት ይቻል ዘንድ በፌዴራልም ሆነ በክልሎች ደረጃ ከሕግ አውጭው፣ ከፍ/ቤቶች፣ ከሕግ ባለሙያዎች፣ ተገቢው ትኩረትና አስተዋጽኦ ይጠበቃል፡፡ እስከዚያው ግን ለአብነት ከላይ በተገለፀው አኳኋን በባዕድ አገር ለአስራ አምስት ዓመታት (ለአንባቢያን መግለጽ በሚቸግር ዝቅተኛ ሥራ) ደፋ ቀና ብላ ያፈራችውን ንብረት (ሌላ ሴት አግብቶ ከነበረው) የቀድሞ ባሏ ጋር ለመካፈል በተገደደችው ሴት ላይ የተከሰተው ኢርትአዊና ኢፍትሐዊ ሁኔታ በሌሎችም ዜጐቻችን ላይ እንዳጠላ ይቆያል፡፡ ■